# ጥናት አንድ ሉቃስ 1፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሉቃስ የመጀመሪያው ታሪክ ጸሐፊ እንዳልነበረ የምናውቀው በቁ 1 ላይ ‹‹…ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸውን ያህል ጽፈውት ይገኛል፡፡›› በማለት ስለሚናገር ነው፡፡ ለሃዋርያቱ የሰጣቸው ሁለት ስያሜዎች፤ የመጀመሪያው ‹‹የዓይን ምስክሮች›› የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹የቃሉ አገልጋዮች›› የሚል ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች በተለይም የዓይን ምስክሮች የሚለው ሃሳብ የስሚ ስሚ ሳይሆን በዚያው በሥፍራው ተገኝቶ በአይኑ ካየ ሰው በላይ ሁኔታውን ሊተርክ የሚችል ሰው ሊኖር ስለማይችል ነው፡፡
2. ሉቃስ እንዲያው የሰማውን ታሪክ ዝም ብሎ ያሰፈረ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን ሁሉን ነገር ከመሰረቱ አንስቶ በጥንቃቄ በመመርመር ካረጋገጠ በኋላ እያንዳንዱን ነገር ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ እንደጻፈ ይነግረናል፡፡ ቁ4 እንደሚነግረን ቴዎፍሎስ የተማረው ነገር በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ነገር መሆኑን እንዲያውቅና ልቡ እንዲያርፍ ነው፡፡
3. እነዚህ ሁለት ሰዎች ሁለቱም የጌታን ትዕዛዝና ሥርዓት ሁሉ የሚጠብቁ እንደነበሩ፣ ያለነቀፋ የሚኖሩ እንደነበሩና፣ በእግዚአብሄር ፊትም በጽድቅ የሚመላለሱ እንደነበሩ ይነግረናል፡፡ ስለ እነዚህ ሁለት ሰዎች ይህ ክፍል በተጨማሪ የሚናገራቸው ነገሮች፤ አንደኛው አልሳቤጥ መካን እንደነበረች ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በዕድሜ የገፉ መሆናቸውን ነው፡፡
4. መልዓኩ ለዘካርያስ የተገለጠለት በምድቡ ተራ ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ዕጣን በሚያጥንበት ጊዜ ላይ ነበረ፡፡ በተለይ ቁ18ትን ሳነብ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ተስፋ ቆርጠው መጸለያቸውን ያቆሙ ይመስለኛል፡፡ ልጅ ባለመውለዳቸው አኩርፈው እንዳልተቀመጡ የምናውቀው፤ በቁ6 ላይ ከምናየው መንፈሳዊ ህይወታቸው በሰውም ሆነ በእግዚአብሄር ፊት በመልካም መኖራቸውና በተሰጣቸውም አገልግሎት መትጋታቸው ይህንን ያረጋግጥልናል፡፡
5. በቤተሰቡ ተድላና ደስታ ያመጣል፣ ለብዙዎች ደስታ ይሆናል፣ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናል፣ የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፣ በእናቱ ማህጸን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል፣ ብዙዎችን ወደጌታ አምላካቸው ይመልሳል፣ በኤልያስ መንፈስና ሃይል በጌታ ፊት ይሄዳል፡፡
6. ለጥያቄው መልስ አላገኘም፡፡ ቁ20ን ስናነብ መልዓኩ ገብርኤል የዘካርያስን አነጋገር እንደ አለማመን አድርጎ ነው የወሰደው፡፡ ይህ አነጋገር የሚያስተምረን፤ የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል እኛ በፈለግንበት ወይም በወሰነው ሰዓት ሳይሆን የእግዚአብሄርን ሰዓት ጠብቆ መፈጸሙ እንደማይቀር ያስተምረናል፡፡
7. እኔ እንደሚመስለኝ በአካባቢው ያለው ሰው ሁሉ ይህ ሰው በእግዚአብሄር ፊት በጽድቅና በቅድስና የሚመላለስ መልካም የህይወት ምስክርነት የነበረው ሰው ስለሆነ ከቅስፈት ይልቅ ራዕይን ማሰብ ያስቻላቸው ይመስለኛል፡፡
8. እነዚህ ረጅም ዘመናት ለኤልሳቤጥ ቀላል ጊዜ እንዳላሳለፈች፤ በተለይም ደግሞ የልጅ አለመውለድ ነገር በዚያ ህብረተ ሰብ መሃል ከእግዚአብሄር በረከት እንዳለማግኘትና በእርሱ ተቀባይነት ማጣት ሆኖ ስለሚታይ ዘመኗን ሁሉ የሰዎች መሳለቂያ በመሆን የኖረች ሳይሆን እንደማይቀር በቁ25 ላይ ከምትናገረው አነጋገሯ መረዳት እንችላለን፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ ኤልሳቤጥ ዮሐንስ የተወለደው እነርሱ በእግዚአብሄር ፊት መልካም ህይወት ስለኖሩ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሀሄር ምህረት የተነሳ እንደሆነ ሙሉ ለሙሉ የገባት ሴት እንደሆነች እንረዳለን፡፡
9. የነዚህን የሁለት ሰዎች ህይወትና የሚያልፉበትን ሁኔታ ደግሞ የሚያይ ሰው በአዕምሮው ሊጠይቅ የሚችለው ጥያቄ፤ እንደዚህ በጽድቅና በቅድስና እየኖሩ እግዚአብሄር ለምን በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፉ ይፈቅዳል የሚለው ጥያቄ በአዕምሯችን ውስጥ ሊያልፍ እንደሚችል አስባለሁ፡፡

## ጥናት ሁለት ሉቃስ 1፡26-56 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዮሐንስና ኢየሱስ በእድሜ የሚበላለጡት በስድስት ወር ብቻ ነው፡፡ በዕብራዊያን 1፡14 ላይ መላዕክት የእግዚአብሄር መልዕክተኞችና ቅዱሳንን ለማገልገል የሚላኩ እንደሆኑ ሲናገር፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ውስጥ ደግሞ መልአኩ ገብርኤል ልክ በዕብራውያን እንደተነገረው በእግዚአብሄር ተልኮ ቅዱሳንን ሲያገለግል መታየቱ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚደጋገፍና ራሱን በራሱ ሊተረጉም የሚችል እንደሆነ እናያለን፡፡
2. ማርያም እጅግ የተወደደች ይላታል፣ ጌታ ከእርሷ ጋራ እንደሆነ ይነግራታል፣ በተጨማሪም ደግሞ ማርያም የተባረከች እንደሆነች ያረጋግጥላታል፡፡ እነዚህ ሶስቱም ነገሮች እግዚአብሄር ራሱ በእርሷ ላይ ስላለው አመለካከትና አሰተሳሰብ ላይ የሚያተኩሩ እንጂ እርሷ ካደረገችው ነገር ጋራ የሚያያዝ ምንም የማየው ነገር የለም፡፡ ማርያምን ያስደነገጣት እኔ እንደሚመስለኝ እሷ ራሷን የምትመለከትበትና እግዚአብሄር እርሷን የሚመለከትበት መንገድ ጭራሽ የማይገናኝ ሆኖ ስለታያት ይመስለኛል ሁኔታው አልገባጠም ብሎ ያስደነገጣት፡፡
3. ማርያም እንዳትፈራ ምክንያት አድርጎ መልአኩ የነገራት ‹‹በእግዚአብሄር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና›› የሚለውን ሃሳብ ነው፡፡ በቅርቡ በህይወቷየሚከናወኑትና በመልአኩ የተነገሯት ሶስት ነገሮች፤ እንደምትጸንስ፣ ወንድ ልጅ እንደምትወልድና፣ የልጁንም ስም ኢየሱስ እንደምትል ነው የተነገራት፡፡ ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅ ይባላል፣ የዳዊት ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘለዓለም ይነግሳል፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም የሚሉት ናቸው፡፡
4. የማርያም ጥያቄ እንዳለማመን አልተወሰደም፤ ይህንንም የምናውቅበት ምክንያት ዘካርያስ ለጠየቀው ጥያቄ እንኳን መልስ አልተሰጠውም፤ ለማርያም ጥያቄ ግን መልአኩ ሁኔታዎቹን አንድ በአንድ በማስረዳት መልስ ሲሰጣት እንመለከታለን፡፡ ማርያም ያልተረዳችውንና ጥያቄ የሆነባት ነገር መልስ ከሰማች በኋላ ነገሩ ቢገባትም ባይገባትም እግዚአብሄር ፈቃዱን በእርሷዋ ውስጥ እንዲፈጽም ረሷን አሳልፋ ስትሰጥ እንመለከታለን፡፡
5. እነዚህ ልጆች የተአምራት ልጆች የሚባሉበት ምክንያት፡ የማርያም ልጅ ያለወንድ ከድንግል ሴት በመወለዱ ሲሆን፤ የኤልሳቤጥ ልጅ ደግሞ የመውለጃ እድሜ ካበቃ በኋላ ከሞተ ሰውነት የተወለደ ልጅ ስለሆነ ነው፡፡
6. የመልዓኩ የገብርኤል ሰላምታ በማርያም ህይወት ውስጥ የፈጠረው የፍርሃትና የድንጋጤ ስሜት ሲሆን፤ የማርያም ሰላምታ ግን በኤልሳቤጥ ቤት ውስጥ የፈጠረው የደስታ ስሜት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ዘመዳሞች እንደመሆናቸው ከዚህ ቀደም ቤቷ ስትገባ ይዛ ያልመጣችውና ዛሬ ወደ ኤልሳቤጥ ቤት ይዛ የመጣችው አዲስ ነገር ቢኖር በማህጸኗ የተሸከመችው ፍሬ ኢየሱስ ስለነበረ ነው ደስታ በደስታ ያደረገው፡፡
7. ኤልሳቤጥ ጌታ ብላ የተቀበለችው ገና በማርያም ማህጸን ውስጥ የነበረውን ኢየሱስን ነው፡፡ ኤልሳቤጥ ማርያምን የምታየው ከሴቶች መሃል ኤልሳቤጥንም ጨምሮ ማለት ነው የተባረከች እንደሆነች፣ የማህጸኗ ፍሬ የተባረከ እንደሆነ እና፣ የጌታዋ እናት እንደሆነች አድርጋ ነው የምታያት፡፡
8. በ1ኛ ዮሐ 3፡1 ላይ ስናነብ እኛ አማኞች በእግዚአብሄር እጅግ የተወደድን መሆናችንን እናያለን፤ በማቴ 28፡20 ላይ ጌታ እስከ ዘለዓለሙ ከእኛ ጋራ እንደሆነ የሚነግረን ሲሆን፤ ኤፌ 1፡3ትን ደግሞ ስንመለከት በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ በረከት ሁሉ የተባረከን ሰዎች መሆናችንን እናያለን፡፡ ስለዚህ እነዚህንና የመሳሰሉትን ሌሎችም የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ስናነብ በክርስቶስ በኩል የዚህ ሁሉ መልካም ነገር ተካፋዮች እንደሆንን መረዳት እንችላለን፡፡

# ጥናት ሶስት ሉቃስ 1፡46-80 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ማርያም በዝማሬዋ ውስጥ ከጠቀሰቻቸው የእግዚአብሄር ባህርያት መሃል ሃያል፣ ቅዱስ፣ እና መሃሪ የሚሉትን የምናነብ ሲሆን ሶስቱም በቁ49-50 ውስጥ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ እግዚአብሄር ይህንን መልካም ነገር ለማድረግ የተነሳሳበት ዋነኛ ምክንያት ሆኖ በቁ55 ላይ የተነገረው፤ ለአብርሃምና ለዘሩ የገባውን የተስፋ ቃል ለመጠበቅ ነው። በነዚህ ሁለት ነገሮች መሃል ምናልባትም ከሁለት ሺህ ያላነሱ አመታት አልፈዋል።
2. ጎረቤቶችዋና ዘመዶችዋ በኤልሳቤጥ ህይወት የሆነውን ነገር የጌታ ታላቅ ምህረት ድንቅን ነገር እንዳደረገላት አድርገው ነው የተቀበሉት። ለኤልሳቤጥ እግዚአብሄር ባደረገው ነገር ጎረቤቶችዋና ዘመዶችዋ የተሰማቸው የደስታ ስሜት ስለነበረ ከእርስዋ ጋራ በመደሰት የደስታዋ ተካፋይ ሲሆኑ ነው የምንመለከተው።
3. ዘካርያስ የልጁ ስም እንዲሆን የፈለገው ዮሐንስ ነው። አባቱና እናቱ የልጁን ስም አስመልክቶ ሊያስማማቸው የቻለው ነገር እግዚአብሄር ስለተናገራቸው ነው። በአባትየው ስም አወጣጥ ላይ በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች ያስደነቀው ነገር፤ አባትና እናት ሳይነጋገሩ ሁለቱም አንድ አይነት ስም በማውጣታቸው ነው።
4. እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ የዘካርያስ አፉ የተዘጋው ባለማመን ምክንያት እንደሆነ ሁሉ፤ አሁንም በመታዘዙ አፉ እንደተከፈተለት ማየት እንችላለን። ይህ ሰው አንደበቱ እንደተከፈተለት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገነዘብ የተናገረው የምስጋና ንግግር ነበረ። እኔ ከዚህ ሁኔታ የምማረው ነገር ቢኖር፤ እግዚአግሄርን አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት እንዳልው ሁሉ እርሱን መታዘዛችንም ሊያመጣ የሚችለው በረከት እንዳለ ያስተምረኛል።
5. የማርያም ዝማሬና የዘካርያስ ትንቢት የሚመሳሰሉባቸው ነጥቦች፤ ሁለቱም ሰዎች እግዚአብሄር እያደረገ ያለው ነገር ለእስራኤል ምህረቱን ለማሳየት እንደሆነ ሲናገሩ፣ በተጨማሪም ደግሞ እግዚአብሄር ይህንን ያደረገው ለአባቶች በተለይም ለአብርሃም የገባውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም እንደሆነ ሁለቱም ይናገራሉ።
6. ይህ የዘካርያስ ትንቢት በዮሓንስ ህይወት ውስጥ ሊፈጸም የሚችልበትን መንገድ ማየት የምንችለው፤ በቁ76 ላይ ትንቢቱን ቀጥለን ስናነብ እንደምንመለከተው ዮሓንስ ለኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና አገልግሎት በነብይነትና በመንገድ ጠራጊነት እንዲያገለግል የተመረጠ ሰው በመሆኑ በቁ74 ትና 75 ላይ ስለጌታችን ለተነገረው ትንቢት በተዘዋዋሪ መንገድ የትንቢቱ መፈጸሚያ ሊሆን እንደሚችል፤ በተለይም ደግሞ ቁ77 እንደሚነግረን የመዳንን እውቀት በመስጠት ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን።
7. ዘካር ያስ ከሚሆኑት ነገሮች ሁሉ በስተጀርባ እያየ ያለው ነገር የእግዚአብሄርን ምህረትና ቸርነት እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም። ይህ ሰው የታየው፡ በጨለማ ለሚኖሩትና በሞት ጥላ ውስጥ ላሉት እንዲያበራ የንጋት ጸሓይ ከሰማይ እንደወጣ፣ በተጨማሪም ደግሞ እግሮቻቸውም ወደ ሰላም መንገድ እንዲያመራ ጌታ በቸርነቱ ብርሃንን ከሰማይ እንደሰጣቸው ማየት ችሏል።
8. እነዚህ ሰዎች ሲያደርጉ የምናየው ለተወለደው ልጅ ባህልን የተከተለ ስም ለማውጣት ሲሞክሩ ነው። በዚህን ጊዜ ማር ያም የነበሯት አማራጮች አንደኛው እነርሱ ያሏትን ተከትላ በአባቱ ስም ዘካር ያስ ማለት ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር በመልአኩ በኩል የነገራትን ስም በመቀበል ኢየሱስ ብላ መጥራት ነበር፤ እርሷ የመረጠችው ግን የእግዚአብሄርን ትእዛዝ መከተል ነው።

# ጥናት አራት ሉቃስ 2፡1-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናያቸው ተዋናኞች፡ አውግስጦስ ቄሳር፣ ዮሴፍ፣ ማርያም፣ ትንሽ ህጻን ልጅ፣ እረኞች፣ የጌታን መልዓክ እና የሰማይ ሰራዊትን እንመለከታለን። ለማርያምና ለእጮኛዋ ለዮሴፍ ጉዞ ምክንያት የሆናቸው ነገር ከንጉሱ ቆጠራን አስመልክቶ የወጣው ዐዋጅ ነበረ።
2. ዐዋጁን በዚህ መልኩ ማየት የምንችልበት ምክንያት፤ በተለይም ዮሴፍ ለመውለድ ጥቂት ቀናት የቀራትን ሚስቱን ግዴታ ያለበትና የንጉስ ዐዋጅ ባይሆንበት ኖሮ የዚህን ያህል መንገድ ጉዞ ተጉዞ ሊያሰኬደው የሚችል ምንም ነገር እንደማይኖር ለማንም ግልጽ ነው፤ ከዚህም ደግሞ በላይ የሚያስገርመው መሲሁ መወለድ ያለበት በቤተልሄም እንደሆነ በትንቢት መነገሩና አዋጁም ሰዎች ትልቅ ወደሆነና በአካባቢያቸው ወዳለ ከተማ ሳይሆን ወደ ትውልድ ቦታ እንዲሄዱ ማስገደዱ የትንቢት ማስፈጸሚያ መንገድ አድርጎ እግዚአብሄር የንጉሱን ልብ በምሳ 21፡1 እንደተነገር ሲያደርግ ነው የሚታየው።
3. ይህ የንጉስ አዋጅ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል ብዬ የማምነው ትንቢት፤ በትንቢት ሚክያስ 5፡2 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሄም እንደሚወለድ የተነገረው ትንቢት በዚህ ክፍል ተፈጻሚ ሆኗል። መልአኩ ለዘካር ያስ ሲናገረው እርሱ በእግዚአብሄር አገልግሎት ላይ ሲሆን፣ እረኞቹ ግን መልአኩ ሲናገራቸው የእለት ተእለት ተግባራቸውን በማከናወን ላይ ነበሩ፣ ዘካር ያስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ብቻውን ሲሆን እረኞቹ ግን ከአንድ በላይ እንደነበሩ ይታያል፣ ሁለቱም ፍርሃት ሞልቶባቸው ነበረ። እግዚአብሄር መንፈሳዊ በሚመስለን ነገር ላይ ተሰማርተን ስንሰራ ብቻ ሳይሆን በእለት ተግባራችንም ተሰማርተን ስንሰራ ሊናገረን እንደሚችል እንማራለን።
4. በእረኞቹ አጠገብ ቆመ፣ የጌታ ክብር በዙሪያቸው አበራ፣ ታላቅ ፍርሃት ያዛቸው፣ እንዳይፈሩ ተነገራቸው፣ መልአኩ ተል ተልእኮውን ለእረኞቹ ሲያስተዋውቅ "ለህዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ አምጠቼላችኋለሁ" በማለት ነው የተናገረው። የዚህ ህጻን መወለድ የምስራች ሆኖ መነገሩና ለህዝብ ሁሉ ደስታ የሚሆንበት ምክንያት በቁ11 ላይ እንደምናነበው ህዝቡን ሁሉ ከታሰረበት ሃጥያት የሚያላቅቅና የሚያድን መድሃኒት ስለሆነ ነው።
5. እረኞቹ ያጋጠማቸው ሌላ ነገር፤ ብዙ የሰማይ ሰራዊት አስቀድሞ ከተገለጠላቸው መልአክ ጋራ በመሆን እግዚአብሄርን ሲያመሰግኑት ተመለከቱ። እረኞቹ ያዩትንና የተገለጠላቸውን ነገሮች በሙሉ ጌታ እግዚአብሄር የገለጠላቸው ነገር እንደሆነ መገንዘባቸውን በቁ15 ላይ ከተናገሩት አነጋገር መረዳት ይቻላል። ይህንን ማወቅ የሚቻለው በቁ15 ስለመሄድ ሲነጋገሩ "ይህንን የሆነውን ነገር እንድናይ" በማለት የተከናወነና ያለቀለት ነገር አድርገው እንደተቀበሉት ይታያል።
6. እረኞቹ በመጀመሪያ ደረጃ ያደረጉት ነገር ፈጥኖ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ነው፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የተባለውን ህጻን ካዩት በኋላ እግዚአብሄር የገለጠላቸውን ነገር እዚያ ለተገኙት ሰዎች መንገር ነበረ። ብዙዎቹ በሰሙት ነገር መደነቃቸውን ሲነግረን፤ ማርያም ግን የሰማችውን በልቧ ይዛ ታሰላስለው እንደነበረ እናነባለን።
7. ሁለቱም ስም የወጣላቸው በመገረዢያቸው ቀን ላይ ነበረ፤ የዮሓንስ ስም ሲወጣ ጎረቤትም ለመሳተፍ ሞክሮ ነበረ፣ የኢየሱስ ስም ሲወጣ ግን ማንም ሌላ ስም ለመስጠትና በባህሉ መሰረት ስም ይሰጠው ብሎ ሲጠይቅ አይታይም። ማርያምና ዮሴፍ ወደዚህች ከተማ መሄድ የነበረባቸው ምክንያት የጌታ ህግ እንዲያደርጉ የሚጠይቀው ነገር ስለነበረና ያንን ህጉ የሚጠብቅባቸውን ነገር ለመፈጸም ነው።
8. እግዚአብሄር ከተናገራቸው ነገር ሁሉም ነገር እንደተነገራቸው ሆኖ ነው ያገኙት። ይህ ያዩት ታላቅ መገለጥ ከተከናወነ በኋላ ተመልሰው እንደሄዱ የሚነግረን አስቀድመው ይሰሩት ወደነበረው የእረኝነት ስራቸው ነው። በነበሩበት ሁኔታ ቢቆዩ ደስ እንደሚላቸው አልጠራጠርም፤ ምክንያቱም አይተውና ተለማምደው የማያውቁት ሰማያዊ ልምምድ ውስጥ መሆናቸውና በተጨማሪም በጎቹ የት ገቡ የት ወጡ ከሚለው ሃሳብ አርፈው ስለነበር ነው።

# <u>ጥናት አምስት ሉቃስ 2፡25-52 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ስምዖን ጻድቅ ሰው ነበረ፣ ትጉህ ሰው ነበረ፣ የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅ ሰው ነበረ፣ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያደረ ሰው ነበረ። ማንኛውም የአዲስ ኪዳን አማኝ መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ ከስምዖን የሚለይበት ዋነኛው መንገድ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያደረበት ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያደረበትና መኖሪያው ያደረገው መሆኑ ነው። (1ኛ ቆሮ 3፡16)
2. በቁ25፣ 26 እና 27 ውስጥ በእያንዳንዱ ቁጥር ውስጥ አንዳንዴ፤ በአጠቃላይ ሶስት ጊዜ ተጠቅሶ እንመለከታለን። ከክፈሉ እንደምረዳው ስምዖን የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅ ሰው ስለነበረ ይመስለኛል መንፈስ ቅዱስ እርሱን መርቶ ለእስራኤል መጽናናት ወደሆነው ወደ ኢየሱስ መርቶ ያመጣው። ስምዖንን ለረጅም ዘመን ሲጠባበቀው የነበረውን ኢየሱስን ባቀፈበት ጊዜ እጅግ ታላቅ የሆነ የደስታ ስሜት እንደተሰማው ይመስለኛል።
3. ቁ26ትን ስናነብ ጌታ ለዚህ ሰው የገባለትን ቃል ኪዳን እናያለን፤ ይህም የጌታን መሲህ ሳያይ እንዳማይሞት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ተነግሮት ነበረ። ኢየሱስ ለአህዛብ መገለጥን የሚሰጥ ብርሃን እንደሆነና ለእስራኤል ደግሞ ክብር እንደሆን ይናገራል። እግዚአብሄር ለህዝብ ደህንነት የሚሆነውን ኢየሱስን ለማየት ካስቻለው እንደሚበቃውና አሁን በሰላም ሊሰናበት ዝግጁ መሆኑን ነው ሲነግረው የምናየው።
4. ህጻኑ በእስራኤል ለብዙዎች መነሳትና መውደቅ ምክንያት ይሆናል፣ ክፉ ለሚያስወሩበት ምልክት ይሆናል፣ የብዙዎች የልብ ሃሳብ የተገለጠ ይሆናል፣ የማርያም ነፍስ ደግሞ በሰይፍ ይወጋል። ይህ አባባል እኔ እንደምረዳው በውስጣቸው ክፋት የሞላ፣ ጽድቅን የሚጠሉና የእግዚአብሄር ፍርሃት የሌለባቸው ሰዎች ኢየሱስን ራሱን፣ ትምህርቱንና ስራውን ሁሉ በመጥላት ወደ ማሳደድና እስከ መግደል ድረስ እንደሚደርሱ ሁሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በልባቸው የእግዚአብሄር ፍርሃት የሞላ፣ ጽድቅን የሚጠሙና በኢየሱስ ትምህርትና ከሚያደርጋቸው ተአምራቶች የተነሳ ከእግዚአብሄር ጋራ የሚታረቁ ሰዎች እንደሚኖሩ ይጠቁመናል።
5. የሴቲቱ ስም ሃና ይባላል፣ ከአሴር ወገን ነች፣ የፋኑኤል ልጅ ነች፣ ነብይት ነበረች፣ አርጅታ ነበረ፣ ከባሏ ጋራ የኖረችው ለሰባት ዓመታት ብቻ ነበረ፣ እድሜዋ ሰማንያ አራት አመት ነበረ፣ በቀንና በሌሊት በጸሎት የምታገለግል ነበረች፣ የኢየሩሳሌምን መቤዥት የሚጠባበቅ ሰው የማውቀው በዚሁ በቁ25 የተመለከትነው ሰው ስምዖን ነው። ጾምንና ጸሎትን በዚህ ስፍራ የሚያቀርብልን እንደ አገልግሎት አድርጎ ነው።
6. ይህ ክፍል ስለእነዚህ ሰዎች የሚጠቁመን ነገር ስለመንፈሳዊ ህይወታቸው ግድየለሾች እንዳልሆኑና የእግዚአብሄርን ህግና ስርዓት በጥንቃቄ ለመጠበቅ የሚተጉ ሰዎች እንደነበሩ ያሳየናል። ህጻኑ በስጋዊ ሰውነቱ እያደገና እየጠነከረ እንደሄደ፤ በውስጡ ደግሞ በጥበብ እንደተሞላ፣ የእግዚአብሄርም ጸጋ በእርሱ ላይ እንደነበረ እናነባለን።
7. ኢየሱስ ለእናቱ ጥያቄ የመለሰው መልስ “ለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?” በማለት ነበረ። አባትና እናቱ ኢየሱስ የተናገረው አነጋገር ግራ ያጋባቸውና ያልገባቸው ምናልባት አባቴ እያለ የሚናገረው ለእነርሱ እግዚአብሄርን እንደ አባቱ አድርጎ የመናገሩ ሁኔታ ሊዋጥላቸው ስላልቻለ ሳይሆን አይቀርም እላለሁ።
8. ኢየሱስ የተገኘው በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲሆን፣ ሲያደርግ የነበረውም በመምህራኑ መካከል ተቀምጦ ጥያቄና መልስ ሲያካሂድ ነበረ። በተለይ በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ያደርግ የነበራቸው ሶስት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ማዳመጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ጥያቄ መጠየቅ፣ ሶስተኛው ደግሞ ለጥያቄዎቻቸው መልስ መስጠት ነበረ።
9. በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ቅድሚያ ሰጥቶት የምመለከተው ነገር እነርሱ የሚናገሩትን ሃሳብ ማዳመጥ ነበረ። ምሳ 18፡13 ላይ “ከማዳመጡ አስቀድሞ የሚመልስ ቂልነትና እፍረት ይሆንበታል” እንደሚል መልስ ለመስጠት ከመቸኮል በፊት ማዳመጥና ጥያቄ መጠየቅ ጥበብ መሆኑን እማራለሁ።

# <u>ጥናት ስድስት ሉቃስ 3፡1-37 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ዮሓንስ አገልግሎቱን የጀመረበትን ጊዜ ለማወቅ አስቸጋሪ የማይሆንበት ምክንያት እስከ ቁ2 ኢጋማሽ የተዘረዘሩት ሃሳቦች በሙሉ ያ ጊዜ ምን ላይ እንደዋለ የሚናገሩ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በማስረጃነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። ዮሓንስ ይዞ የተነሳው መልእክት ቁ3 ላይ እንደምናነበው ለሃጥያት ስርየት የሚሆን የንስሃ ጥምቀት መጠመቅ እንደሚኖርባቸው ማስገንዘብ ነበረ።
2. የንስሃ ጥምቀት ለመጠመቅ ወደ ዮሐንስ የመጡት ሰዎች በተጨማሪ የተጠየቁት ነገር፤ ለንስሃ የሚገባ ፍሬ እንዲያፈሩ ነው። ዮሐንስ ይህንን ሲል፤ ዝም ብሎ ውሃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ብቻ ሳይሆን እውነትም ከልባችሁ ንስሃ መግባታችሁን የሚረጋገጥበትና የሚታወቅበትን መልካም ፍሬ በህይወታችሁ አሳዩ ማለቱ ነው። ይህ አነጋገር ኢየሱስ በዮሐ 8፡33 ላይ እንደተናገረው በስጋ ከአብርሃም ዘር በመሆን ብቻ ከእግዚአብሄር ጋር መልካም ግንኙነት እንዳለ አድርጎ በማሰብ ራስን ጻድቅ አድርጎ የማሰብ ችግር ነው።
3. በዚህ ክፍል ህዝቡ የንስሃ ፍሬ ለማፍራት ልቡ የተዘጋጀ ነበረ ማለት የሚያስችለን ነገር የጠየቁት ጥያቄ ሲሆን፤ ይህም ጥያቄ "ሕዝቡም ታዲያ ምን እናድርግ" ብለው ጠየቁት በማለት ይነግረናል። መልሱ "ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል፣ ምግብ ያለውም እንዲሁ ያድርግ" የሚል ነው። ዮሓንስ ይህንን ሲል ሰው ከሁለት በላይ ልብስ አይኑረው ማለት ሳይሆን፤ ሌላው አንድ ልብስ ሳይኖረው ራቁቱን እየሄደ እኛ ትርፍ ማስቀመጥ ፍቅርን እንደማያመለከት ሲናገር ነው።
4. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናያቸው የንስሃ ጥምቀት ለመጠመቅ የመጡት የሰዎች፤ ህዝቡ የተባሉት፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ወታደሮች የሚላቸው ይገኙበታል። ቀረጥ ሰብሳቢዎቹ ያደርጉት የነበረው ነገር ከታዘዙት በላይ ቀረጥን መሰብሰብ ነበረ። እነዚህ ሁለት የህብረተሰብ ክፍል የሆኑ ሰዎች ከሮማውያን ጥላ ስር ተጠልለው ህዝቡን በማስጨነቅ የኖሩ፣ ይህ ድርጊታቸውም በህዝቡ ዘንድ በጥላቻ እንዲታዩ የሆኑ ስዎቸ ስለሆኑ ይመስለኛል።
5. አንድ ወታደር ንስሃ ገብቶ የንስሃ ፍሬ አፍርቷል ለማለት የሚያስችለን፤ በቁ14 ላይ ዮሓንስ እንዲወስዱ የነገራቸውን እርምጃ ሲወስዱ ነው፤ ይኸውም የማንንም ገንዘብ በግፍ አለመንጠቅ፣ ሰዎችን በሃሰት አለመክሰስና፣ ከሌሎች ሳይዘርፉ ደመወዛቸው እንዲበቃቸው የሚሉት ናቸው።
6. ከቁ15 እንደምንረዳው፤ ይህ ሰው እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? የሚለው ጥያቄ በህዝቡ ሃሳብ ውስጥ ይመላለስ ነበረ። ይህ ሰአት ለእግዚአብሄር ባርያ  አደገኛ ሰኣት የሚሆንበት ምክንያት በህዝብ ሁሉ ልብ የክርስቶስ ቦታ ሲሰጠው አዎን እኔ እርሱ ክርስቶስ ነኝ የሚለውን የክብር ወንበር የመቀበል ፈተናን ዮሓንስ በማለፍና በማሸነፍ አይ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም በማለት ለህዝቡ የእርሱን ትክክለኛ ቦታ መናገር ነበረበት።
7. እርሱ ከዮሐንስ የሚበልጥባቸው መንገዶች፤ ዮሐንስ በውሃ ሲያጠምቅ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት እንደሚያጠምቅ፣ ኢየሱስ ከእርሱ እንደሚበረታ፣ የኢየሱስን የጫማ ማሰሪያ መፍታት እንደማይገባው ተናግሯል፣ ኢየሱስ ፍርድ የመፍረድ መብት ያለው ነው። ዮሐንስ ያደረገውን ድርጊት የወንጌል ሰባኪነትን ስራ እየሰራ እንደነበረ ነው የሚናገረው።
8. ዮሐንስ ሄሮድስን ስለሃጥያቱ መገሰጹ የእግዚአብሄርን ህግ መተላለፍ ነው ብዬ አላምንም፣ ምክንያቱም ማንኛውም ንጉስም ሆነ ባለስልጣን በእግዚአብሄር አይን ከማንኛውም ተራ ሰው ተለይቶ ስለማይታይ በጽድቅ የመኖርና በጽድቅ የመፍረድ ሃላፊነት ስላለበት ያንን ሃላፊነቱንና ግዴታውን መናገር ትክክለኛ የእግዚአብሄር ሰው ሃላፊነት እንደሆነ አምናለሁ፤ እግዚአብሄር የሰውን ፊት አይቶ አያዳላምና።

# ጥናት ሰባት ሉቃስ 4፡1-19 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. “የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፣ በአንተ ደስ ይለኛል” የሚል ምስክርነት ነው ከእግዚአብሄር ዘንድ ያለው። መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ወደ ምድረበዳ የወሰደበት ምክንያት በሰይጣን ለአርባ ቀናት ያህል እንዲፈተን በማለት ነው። እንደ እኔ አስተያየት ከሆነ ይህ ኢየሱስ ያለፈበት ሁኔታ ለእኛ ሊያስተምረን የሚችለው ነገር፤ በጠላት ስንፈተንና ሁኔታዎች እኛ እንደምንፈልጋቸው ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ እግዚአብሄር እንደተወንና እንደማይወደን አድርገን ማሰብ እንደማይኖርብን፤ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ ራሱ ከኢየሱስ ጋራ እንደነበረ ከእኛም እንደማይለየን ማሰብ እንደሚኖርብን ነው የሚገባኝ።
2. ኢየሱስ በመጀመሪያ የቀረበለት ፈተና “የእግዚአብሄር ልጅ ከሆንህ፣ እስቲ ይህ ድንጋይ እንጀራ እንዲሆን እዘዘው” የሚል ነበረ። የእግዚአብሄር ልጅነቱ እንዲያረጋገጥ የተጠየቀው ተአምራትን በመፈጸም ነበረ። እግዚአብሄር “የምወድህ ልጄ አንተ ነህ” በማለት አረጋግጦለታል።
3. አዎን፣ ምክንያቱም በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ዲያቢሎስን 2ኛ ቆሮ 4፡4 ላይ “የዚህ ዓለም አምላክ” ሲለው በዮሐ 12፡31፣ ዮሐ 14፡30፣ ዮሐ 16፡11 እና የመሳሰሉት ክፍሎች ይህንን ሃሳብ ያስተጋባሉ። ኢየሱስ ስግደት የሚገባው ለእግዚአብሄር ብቻ መሆኑን ነው የሚናገረው። በራዕይ ውስጥ የምናነበው ጥቅስም መልአኩ ለእርሱም እንኳን ቢሆን ስግደት ሊሰጥ እንደማይገባ ለዮሐንስ በማረጋገጥ የተናገረው ሲሆን መላእክትም ቢሆኑ ስግደት እንደማይገባቸው እንማራለን።
4. ይህ ሶስተኛው ፈተና ካለፉት ሁለቱ የሚለየው፤ የቀደሙት ሁለቱ ላይ ዲያቢሎስ ከእግዚአብሄር ቃል በመጥቀስ አልነበረም ፈተናውን ያቀረበው፣ በሶስተኛው ፈተና ላይ ግን ከቃሉ በመጥቀስ ነው የፈተነው። የዚህ ዓይነቱ ፈተና በእኛም ሆነ በማንም ላይ ሲመጣ ከባድ የሚሆነው የሚጠቀሰው የእግዚአብሄር ቃል በጠላት እጅ ገብቶ በማጣመም እየተጠቀመበት መሆኑን ለመረዳት ጥልቅ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የሚጠይቅ በመሆኑ ነው።
5. ቁ13 እንደሚነግረን ኢየሱስን መፈተን ያበቃው “ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ” ነው በማለት ይነግረናል። ይህንን ሲል ዲያቢሎስ ከአሁን በኋላ ኢየሱስን አይፈትነውም ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም በዚያው በቁ13 ላይ ስናነብ “አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ተለየ” ነው የሚለን።
6. በመንፈስ ሃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ ዝናው በአካባቢው አገር ሁሉ ወጣ፣ በምኩራብ አስተማረ፣ ሰው ሁሉ ያመሰግነው ነበር፣ በዲያቢሎስ በተፈተነ ሰዓት ለእያንዳንዱ ፈተና ኢየሱስ ይሰጥ የነበረው ምላሽ የእግዚአብሄርን ቃል ምን ያህል ጥልቀት ባለው መልኩ የሚያውቅ እንደነበረ፤ በተለይም ደግሞ ሶስተኛውን ፈተና የእግዚአብሄርን ቃል ጠቅሶ በፈተነው ሰአት የሰጠውን ከቃሉ የሆነ ምላሽ ስንመለከት ቃሉን ለማስተማር ሙሉ ብቃት ያለው እንደነበረ ማየት እንችላለን።
7. በዛሬው ምንባባችን ውስጥ ኢየሱስ በመግባት በመውጣቱ መንፈስ ቅዱስ የሚመራው እንደነበረ የሚጠቁሙን ክፍሎች፡ ሁለቱ በቁ1 ላይ የሚገኙ ሲሆን አንዱ ደግሞ በቁ14 ላይ ይገኛል። ቁ1 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ እንደተመለሰ ሲነግረን፣ በዚያው ቁጥር ውስጥ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወደ በረሃ ወይም ምድረበዳ እንደወሰደው ይነግረናል። ቁ14ትን ስናነብ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ወደ ገሊላ እንደ ተመለሰ ሲነግረን ቁ18 ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ እንዳለ በማረጋገጥ ይነግረናል።
8. የጌታ መንፈስ በኢየሱስ ላይ በመሆኑ ምክንያት ለድሆች ወንጌልን እንዲሰብክ ተቀብቷል፣ ለታሰሩት መፈታትን፣ ልታወሩትም ማየትን እንዲያውጅ ተልኳል፣ የተጨነቁትን ነጻ እንዲያወጣና የተወደደችውንም የጌታን አመት እንዲያውጅ ተልኳል።

# <u>ጥናት ስምንት ሉቃስ 4፡20-44 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ህዝቡ ስለ ኢየሱስ በጎ እንደሚናገሩ፣ ከአንደበቱ በሚወጣው የጸጋ ቃል ይገረሙ እንደነበረ ስናይ፤ እርሱን በሙሉ ልባቸው እንዳይቀበሉት ትግል የሆነባቸው፤ በሰፈር ውስጥ ያዩት የነበረ፣ ወላጆቹንና ተወልዶ ያደገበትን ሁሉ ማወቃቸው በቀላሉ እንዳይቀበሉት ትግል ሆኖባቸዋል። ኢየሱስ ይህንን ሲል በቁ18-19 ላይ የተነበቡት ነገሮች ሁሉ በእኔ ነው፤ ማለትም ለድሆች ወንጌልን የምሰብከው፣ ለታሰሩት መፈታትን የምሰጠው፣ ለታወሩት ማየትን የምሰጠውና… የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ የምፈጽመው እዚህ ፊት ለፊታችሁ የምታዩኝ እኔ ነኝ ማለቱ ነው።
2. ባለመድሃኒት ከሆንክ ራስህን አድን፣ በሌላ ከተሞች ያደረግኸውን ተአምራት እዚህም በራስህ ከተማ ውስጥ አድርገው ሊሉት ሃሳብ በልባቸው እንዳለ ይነግራቸዋል። ይህንን እውነት ለማስረዳት የተጠቀመባቸው ነብያት ኤልያስና ኤልሳዕ ናቸው።
3. ኤሊያስ በምድር ላይ ከባድ ድርቅ በነበረበት ሰዓት ከአህዛብ ከተማ በሆነችው  በአንዲቱ ከተማ ወደምትገኝ አንድ መበለት እንጂ በእስራኤል ከነበሩት ብዙ መበለቶች ወደ አንዲቱ እንዳልሄደ፤ ኤልሳዕም እንደዚሁ በእስራኤል የነበሩ ለምጻሞች ሳይሆ ከአህዛብ የሆነውን ንዕማንን እንደፈወስ እናነባለን። ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት እናንተ ነብዮቶቻችሁን ትንቃላችሁ፤ ስለዚህም ነብያቱ አድማጭና ተቀባይ ወዳለበት መሄዳቸው አይቀርም የሚል ነው። ይህንን ሲል አድማጮቹ ደስተኞች አልነበሩም (ቁ28)።
4. ኢየሱስ ከናዝሬት ወጥቶ የገባው ቅፍርናሆም ወደምትባል በገሊላ አውራጃ ወደምትገኝ ከተማ ሲሆን፤ የዚህችን ከተማ ስም ያየነው በቁ23 ላይ ከኢየሱስ ንግግር ውስጥ ነው። ከኢየሱስ ትምህርት ህዝቡን ያስደነቀው ነገር ቢኖር፤ ኢየሱስ ሲያስተምር እንደ ፈሪሳውያን ሳይሆን በስልጣን ማስተማሩ ነው መደነቅ የፈጠረባቸው።
5. ኢየሱስ መጥቶ ነጻ እስኪያወጣው ድረስ ጋኔን ያደረበት ሰው ይገኝ የነበረው በምኩራባቸው ውስጥ ነበረ። ጋኔኑ የሚያውቀውና በህዝቡ ፊት የተናዘዘው እውነት፤ ኢየሱስ የአጋንንትን ስራ ሊያፈርስ እንደሚገለጥ፣ ደግሞም እርሱ የእግዚአብሄር ቅዱስ እንደሆን በህዝቡ ሁሉ ፊት ተናግሯል። እነዚህን ሰዎች ያስገረማቸው ነገር፤ ትምህርቱና አጋንንት ሲያዛቸው ታዘው መውጣታቸው ነበረ።
6. በአንደኛ ደረጃ የምናየው ሃይለኛ ትኩሳት የነበረባትን ሴት ሲፈውስ ሲሆን፤ ቀጥሎ ደግሞ የምንመለከተው በተለያየ የህመመ አይነት የተያዙትን ሰዎች አምጥተውለት ሲፈውስ ነው። ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች ለመፈወስ የተጠቀመባቸው ሁለት አይነት መንገዶች ሲሆኑ፤ የመጀመሪያው በሽታውን ገሰጸው ነው የሚለን፣ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በእያንዳንዳቸው ላይ እጁን በመጫን ነበረ የፈወሳቸው። የስምዖን አማት ለተደረገላት በጎ ነገር ምስጋናዋንና ፍቅሯን የገለጠችው በአገልግሎቷ ነበረ።
7. ወደ ገለልተኛ ቦታ ዘወር ማለት ያስፈለገው ምክንያት እንደሚመስለኝና በሌሎች ጊዜያት ከሚያደርገው ልምዱ በመነሳት፤ ከአባቱ ጋራ ለመነጋገር ወይም ለጸሎት እንደሚሆን አልጠራጠርም። ኢየሱስ ተልዕኮው የእግዚአብሄርን መንግስት ወንጌል መስበክ እንደሆነ ነው ለህዝቡ የነገረው።
8. በእኔ አመለከከት እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ከማሞገስ ወደ ጥላቻ በዚህ ፍጥነት ሊያመጣቸው የቻለው ነገር፤ በቁ22 ላይ ያመሰገኑት በቁ18-19 ላይ ተልዕኮውን ሲነግራቸው በመልካም ነገር የተሞላ ስለነበረ በደስታ ሲያስተናግዱት፤ በቁ28-29 ደግሞ ጥላቻቸውን መደበቅ ያልቻሉት እነርሱ የእግዚአብሄርን ነብያት ስለማይቀበሉ ነብያቱ ደግሞ እጃቸውን ዘርግተው በደስታ መልዕክቱን ወደሚቀበሉት ወደ አህዛብ እንደሚሄዱ ስለነገራቸው ነው።

# <u>ጥናት ዘጠኝ ሉቃስ 5፡1-39 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. የመጀመሪያውን ጥያቄ ቢያንስ ሁለት ሰዎች በራሳቸው ቋንቋና አነጋገር ታሪኩን መልሰው እንዲተርኩ ይደረግ። ኢየሱስ መጥቶ በሚያናግራቸው ወቅት እነዚህ አሳ አጥማጆች የነበሩበት ሁኔታ እኔ እንደሚመስለኝ፤ ሞራላቸው ወድቆ፣ በተስፋ መቁረጥ ተሞልተው፣ ምናልባትም ሌሊት ሁሉ በመስራታቸው በድካምና በረሃብ የዛሉ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ እገምታለሁ።
2. በነዚህ ቁጥሮች ላይ ኢየሱስ የሰጣቸው ትዕዛዝ ወደ ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ ብለው መረባቸውን እንዲጥሉ ነው። ይህ ኢየሱስ የሰጣቸው ትዕዛዝ ስሜት የማይሰጥበት ምክንያት፤ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ሰዎች ህይወታቸውን ሁሉ ሲሰሩት የነበረው ስራ ነው፣ ውሃውም በየጊዜው የሚመጡበት የሚያውቁት ውሃ ስለሆነ፣ ኢየሱስ ደግሞ የአሳ ማጥመድ የስራ ልምድ አለመኖሩ፣ ሌሊቱን ሙሉ ያልሞከሩት አይነት ሙከራ ስላልነበረና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሁሉ ምክሩ የማያዋጣ ምክር ይመስላል።
3. እንደተነገራቸው ሲያደርጉ እጅግ በጣም ብዙ አሳ እንደያዙ እናነባለን። ይህንን ተአምር ጴጥሮስና ሌሎቹም አብረው የነበሩት ሰዎች በተመለከቱ ጊዜ መደነቅ እንደሞላባቸው ቁ9 ይነግረናል። ኢየሱስ የሚበሉት አሳ ብቻ ሰጥቶና አስደንቆ ብቻ ሊተዋቸው ስላልፈለገ በቁ10 ላይ ለጴጥሮስ መንፈሳዊ መልዕክቱ ምን እንደሆነ ሲገልጥለት እናያለን፤ ይኸውም ብዙ አሳ ያጠመድከውን ያህል የወደፊት ተግባርህ ሰዎችን ማጥመድ ይሆናል ብሎ ይነግረዋል።
4. ኢየሱስ ዛሬ ያደረገው ነገር ሰዎችን የማጥመድ ስራ ሲጀምር ትምህርት የሚሆነው፤ ሰው በራሱ እውቀትና በራሱ ችሎታ መስራት የማይችለው ነገር እንደሆነና በኢየሱስ ላይ መታመን እንደሚኖርበት ያስተምረዋል እላለሁ። ሰውየው እርግጠኛ የሆነው አንድ ነገር ኢየሱስ መፈወስ እንደሚችል ሲሆን፤ የኢየሱስን ፈውስ አስመልክቶ እርግጠኛ መሆን ያልቻለውና ኢየሱስ ሊያረጋግጥለት የሚያስፈልገው አንድ ነገር ደግሞ ፈቃደኛነቱን ነበረ።
5. ኢየሱስ አገልግሎት ቢበዛበት እንኳን ሊተወውና ሊረሳው የማይችለው ነገር ጸሎት እንደሆነ እናያለን። ኢየሱስን ለፈውስ ያነሳሳው የበሽተኛው ጓደኞች እምነት ነው። ጸሓፍትና ፈሪሳውያንን ያስቆጣው ነገር እግዚአብሄር ብቻ ማድረግ የሚችለውን ነገር ኢየሱስ ለማድረግ መነሳቱ ሲሆን፤ ኢየሱስ ደግሞ ሃጥያትን ለማስተሰረይ መቻሉ አምላክ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።
6. ለነዚህ ሰዎች ጥያቄ የፈጠረባቸው ነገር ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ለምን ከሃጥያተኞችና ከቀረጥ ሰብሳቢዎች ጋራ ይበላሉ የሚል ነው። ፈሪሳውያኑንና ጸሓፍትን እንደጤነኞች አድርጎ ነው ያቀረባቸው፤ ይህ ማለት እነዚህ ሰዎች እውነትም ጤነኞች ናቸው ማለት ሳይሆን ራሳቸውን የሚያዩበትን መንገድ ለመጠቆም እንጂ እነርሱም እንደሌሎቹ ሁሉ ባለመድሓኒት የሚያስፈልጋቸው ናቸው።
7. በዚህ ክፍል ደግሞ የነበራቸው ጥያቄ የዮሓንስ ደቀመዛሙርት የሚጾሙትና የአንተ ደቀመዛሙርት ግን የማይጾሙበት ምክንያት ለምንድነው? የሚል ነበረ። ኢየሱስም በቁ35 ላይ ሙሽራ የሆነው ኢየሱስ ከእነርሱ ጋራ ስላለ መጾም አያስፈልጋቸውም፤ እርሱ ሲሄድ ግን ይጾማሉ አላቸው። ከዚህ አነጋገሩ እንደምንረዳው የኢየሱስ ተከታዮች እርሱ ከእነርሱ በተወሰደ ጊዜ መጾም እንደሚኖርባቸው እንረዳለን።
8. የነጴጥሮስ ጓደኞች ለእርዳታ በተጠሩበት ወቅት የእነርሱ መረብ ምንም እንኳን ባዶውን ቢሆንም ሄደው ጓደኞቻቸውን ለመርዳት በሙሉ ፈቃደኛነት ሲረዷቸው እንመለከታለን። ከነዚህ ሰዎች ድርጊት መማር የምንችለው መንፈሳዊ ትምህርት ቢኖር፤ ሌሎች ሰዎች በህይወታቸው ወይም በተሰማሩበት አገልግሎት ወይም ደግሞ በቤተ ክርስትያናቸው እግዚአብሄር መሳካትን ሲሰጣቸው፤ እኛም ከእነርሱ ጋራ የደስታቸው ተካፋይ የምንሆን እንጂ በቅናት ለማበላሸት የምንጥር እንዳንሆን ያስተምረናል።

# ጥናት አሥር ሉቃስ 6፡1-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ ደቀ መዝሙር በማለት የሚናገረው የታወቁትን አስራ ሁለቱን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎቹን ተከታዮቹን ሁሉ ያጠቃለለ ነው፤ ይህንንም ማለት የሚቻልበት ምክንያት፤ በዚህን ጊዜ ኢየሱስ ገና አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን እንዳልመረጠ ከቁጥር 13 ላይ መረዳት እንችላለን። ደቀ መዛሙርቱ የተከሰሱት እሸት ቀጥፈው በመብላታቸው ሳይሆን፤ ቀጥፈው የበሉበት ቀኑ የሰንበት ቀን በመሆኑ ነበረ።
2. የመጀመሪያ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ዳዊት በተራበ ጊዜ ያደረገውን በ1ኛ ሳሙ 21፡6 ላይ የሰፈረውን ታሪክ ሲሆን፣ ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ፤ የሰው ልጅ ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰንበት ጌታ እንደሆነ በመንገር ነው። “የሰው ልጅ ለሰንበት ጌታዋ ነው።” የሚለውን አነጋገር እኔ የምረዳው፤ ኢየሱስ እርሱ አምላክ ስለሆነና ሰንበትንም የሰጠው እርሱ ስለሆነ ትርጉሙንም ሆነ አፈጻጸሙን እርሱ ሊነግራቸው እንጂ እነርሱ ሊያስረዱት እንደማይችሉ መጠቆሙ ይመስለኛል።
3. ኢየሱስ በምኩራብ የነበረበት ዋነኛው ምክንያት ህዝቡን ለማስተማር ነበረ። ጻህፍትና ፈሪሳውያን ደግሞ በመቅደስ የተገኙበትን ምክንያት ቁ7 እንደሚነግረን ከኢየሱስ ስህተት ሊፈልጉና ሊከሱት ሁኔታን ለመጠባበቅ እንደነበረ እናያለን። ከዚህ ከጻህፍትና ከፈሪሳውያን ድርጊት የምንማረው፤ ወደ ቤተ ክርስትያን የገባ ሰው ሁሉ ከኢየሱስ ሊሰማና ሊማር ብቻ እንዳልሆነ፤ በተጨማሪ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ብቻውን ኢየሱስን ለመፈለግና ከእርሱ ለመማር ናፍቆት እንደማይፈጥር ማየት እንችላለን።
4. ኢየሱስ ለጠየቃቸው ጥያቄ ሊከሱት የተዘጋጁት ሰዎች ምንም ዓይነት መልስ ለመስጠት አልቻሉም፤ የኢየሱስን ጥያቄ ለመመለስ ጻህፍቱና ፈሪሳውያኑ የከበዳቸው ምክንያት ለእኔ እንደሚመስለኝ በሁለቱም አቅጣጫ ቢመልሱ ተሸናፊዎች ስለሚሆኑ ነው፤ በጎ ማድረግ ቢሉ ያለምንም ችግር ኢየሱስ ፈውሱን ሊያካሂድ ነው፤ ክፉ ቢሉ ከእግዚአብሄር ህግ ጋራ ተቃራኒ ሊሆኑ ስለሆነ ነው። በሽተኛው ሲፈወስ ሰዎቹ እጅግ እንደተቆጡ፤ በኢየሱስ ላይ መወሰድ ስለሚኖርበት እርምጃ ውይይት አደረጉ።
5. ያደረገው ቅድመ ዝግጅት ሲጸልይ ማደሩ ነው። ይህንን ያህል ጊዜ ከአባቱ ጋራ ጊዜ አጥፍቶና ተነጋግሮ ይሁዳን መምረጡ እንደ ሰው ሲታይ ያደረገውን ስለምናውቅ  ስሜት አይሰጥም፤ በአንጻሩ ደግሞ ባይመረጥ ለቤተ ክርስትያን ያጎድል ነበረ የምለው ሰው ጴጥሮስ ነው፤ ምክንያቱም አብዛኞዎቹ በወንጌል ውስጥ የተጠየቁትን ጥያቄዎች የጠየቀው ጴጥሮስ ሲሆን ኢየሱስ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ በመስጠቱ ለኛ የተረፉ እንደ ማቴ 18፡21፣ ዮሐ 13፡36-37፣ ዮሐ 21፡21 ማየት እንችላለን።
6. በዚህ ቁጥር ላይ “አብሯቸው” እያለ የሚናገረው በቁ13 ላይ ወደ እርሱ በመጥራት የመረጣቸውን አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ነው። በዚህ ክፍል ላይ የምናያቸው፡ ኢየሱስ፣ አሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት፣ ሌሎቹ እጅግ ብዙ የሆኑት ደቀመዛሙርቱ፣ ከተለያዩ ሥፍራዎች የመጡ ብዙ ህዝብ ሲሆኑ፤ እነዚህ ሁሉ በዚህ የተገኙት ለሁለት ምክንያቶች እንደሆነ ቁ18 ይነግረናል፤ ይኸውም ኢየሱስን ሊሰሙትና፣ ካለባቸው ደዌ ሊፈወሱ ነበረ።
7. እነዚህ እጅግ የሆኑ ህዝቦች ኢየሱስ ከፍሎ የሚመለከታቸው በሁለት ዓይነት ሲሆን፤ እነዚህም ብጹዓን የሚላቸውና ሌሎቹ ደግሞ በተቃራኒው ወዮላችሁ የተባሉት ናቸው። ኢየሱስ ድህነትን፣ ረሃብተኛነትን፣ ወይም የሚያለቅሱ እያለ ሲናገር  በማቴዎስ 5 ላይ እንደተናገረው በመንፈስ ድሆች፣ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ያለውን ዓይነት መንፈሳዊ ገጽታውን ለማሳየት እንጂ እግዚአብሄር የኪስና የሆድ ባዶነትን ወይም የፊት መጨማደድን ለማየት ናፍቆት ኖሮት እንዳልሆነ ሊታወቅ ያስፈልጋል።
8. ይህ ሥፍራ የእግዚአብሄርን እውነት ሰዎች የሚማሩበት፤ ከበሽታቸው የሚፈወሱበት፣ ቃሉ እንደሚለው ደግሞ የጸሎት ቤት ሲሆን፤ ፈሪሳውያኑ ግን ኢየሱስን የማጥመጃና ለመግደልም መመካከሪያ ሥፍራ አድርገው ነው የተጠቀሙበት።

# ጥናት አሥራ አንድ ሉቃስ 6፡27-49 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ "ለእናንተ ለምትሰሙ" ሲል፤ በቁ6-7 ላይ የምናያቸው ፈሪሳውያን ምንም እንኳን ኢየሱስ በምኩራብ ገብቶ እያስተማረ ቢሆንም እነርሱ ግን ለመስማት የተዘጋጁ ሳይሆን ለክስ የመጡ ስለሆነ የእነርሱ ዓይነቶቹን ሰዎች ለመለየት ይመስለኛል። የክርስቶስ ተከታዮች ሊቆጣጠሯቸው የማይችሏቸው ሶስት ነገሮች፡ ጠላት መኖርና አለመኖሩ፣ የሚጠሏቸው መኖር አለመኖራቸው እና ረጋሚ መኖር አለመኖሩ በነርሱ ቁጥጥር ውስጥ አይደለም፤ በእነርሱ ቁጥጥር ውስጥ ያሉት ነገሮች መውደድ፣ መልካም ማድረግና፣ መመረቅ ናቸው።
2. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ የተጠየቀው ጥያቄ "…ምን የተለየ ዋጋ ታገኛላችሁ?" የሚለው ነው። ለተከታዮቹ ያስቀመጠውን መለኪያ ሶስቱንም ጊዜ በማነጻጸር የሚናገረው ሐጥአን ተብለው ከሚጠሩት ጋራ ነው። ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ላይ ተከታዮቹንና የአህዛብን ድርጊት በማነጻጸር እየተናገረ ሊያስተምራቸው የፈለገው ዋነኛ ነጥብ እኔ እንደምረዳው ከሆነ፤ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከአህዛብ ከፍ ያለ ሚዛንና መለኪያ ሊኖራቸው እንደሚገባ ሊያስገነዝባቸው እንደሆነ አምናለሁ።
3. እነዚህን ነገሮች በማድረግ የሚገኙት ሁለት ትርፍ አድርጎ የተናገራቸው ነገሮች፡ ወሮታችን ታላቅ እንደሚሆንና፣ የልዑል ልጆች መባል ናቸው። ልዑል ለክፉዎችም ጭምር ቸር ስለሆነና እርሱ ርህሩህም ስለሆነ፤ የልዑል ልጆች እንዲለማመዱ የታዘዟቸው ለደጎች ብቻ ሳይሆን ለክፉዎችም ጭምር ቸርነትን ማሳየትና፤ ርህራሄን መለማመድ ሁለቱ አባታችንን የምንመስልባቸው ነገሮች ሊሆኑ ይገባል።
4. በሉቃስ 6፡37 ላይ የምናነበው ሃሳብ በማቴ 7፡1-5 ላይ እንዳለው አይነት ግብዝነት የተሞላበትና ራስን አጽድቆ ሌላውን የመኮነን አይነት ፍርድን ነው። በዮሐ 7፡24 ላይ ኢየሱስ የተናገረው ሰዎች እንደ እግዚአብሄርን ቃል እውነት ሳይመላለሱ ሲቀሩ እውነቱን በመጠቆም ወደ ንስሃ ለማምጣት የሚደረግ ነገር አስፈላጊ እንደሆነ የሚጠቁመን ሲሆን፤ የዚህ ዓይነቱን እውነት እንዲለማመዱት ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 5፡12-13 ላይ አንባቢዎቹን ሲያበረታታ እንመለከታለን።
5. ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ላይ እውርን ሊመራ የሚችል ሰው እርሱ ራሱ ማየት የሚችል ዓይናማ ሰው ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ወደፈለገበት ሳይደርስ ሁለቱም ከጉድጓድ ይወድቃሉ ይለናል፤ እንደዚሁም አስተማሪ ነኝ የሚለው ሰው ከእርሱ ሊማር ካለው ሰው በተሻለ እውቀት ደረጃ የሚገኝ ሊሆን እንደሚገባው፤ በዚህም ተማሪው በደንብ ከተማረ አስተማሪው የደረሰበት የእውቀት ደረጃ የመድረስ እድል እንዳለው ያስረዳል። እንደተማሪዎች አስተማሪያችን እውር አለመሆኑን ማረጋገጥና፤ እንደ አስተማሪ እኛ እውሮች አለመሆናችንንና የምንመራቸውን ሰዎች ወደ ሚፈለግበት አድራሻ የምንወስድ መሆናችንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
6. በሰዎች ውስጥ የምናየውን ስህተት ለማስተካከል ወይም ለማረም አስቀድመን በራሳችን ውስጥ የተጋደመውን ምሰሶ፣ ማለትም ትልቅ መስተካከል የሚኖርበትን ነገር ማረም አስፈላጊ እንደሆነ ነው የሚነግረን። አስቀድሞ በዓይናችን ውስጥ ያለውን የተጋደመ ምሰሶ ማስወገድ የሌላውን ጉድፍ አጥርቶ ለማየት ይጠቅማል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በራሱ ዓይን ውስጥ የተጋደመውን ሳያይ በሌላው ጉድፍ ላይ የሚያተኩረውን ሰው ግብዝ በማለት ነው የሚጠራው።
7. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የምናገኘው አንድ ቃል "ፍሬ" የሚለው ነው። ኢየሱስ የዛፎችን ዓይነትና ፍሬአቸውን አስመልክቶ ከተናገረ በኋላ እንደማጠቃለያ ሃሳብ አድርጎ የሰጠው ነገር፤ ከሰዎች አፍ ውስጥ የሚወጣው ክፉም ሆነ መልካም ነገር ልክ እንደዛፍ ፍሬ ከውስጣቸው የመነጨ እንደሆነ ነው የሚያስረዳው።
8. ኢየሱስ ወደ እርሱ የሚመጡትንና ትምህርቱን የሚሰሙትን ሰዎች በሁለት ነው የከፈላቸው፤ የመጀመሪያዎቹን በቁ47 ላይ "ቃሌን ሰምቶ የሚፈጽም" በማለት ሲናገር፣ በቁ49 ላይ ደግሞ "ቃሌን ሰምቶ የማይፈጽም" በማለት ነው ይናገራል።
9. የኢየሱስን ቃል ሰምቶ የሚፈጽም ሰው ቤቱን ለመሥራት መሰረቱን አጥልቆ የሚቆፍርና በዓለት ላይ መሰረቱን የሚመሰርትን ሰው አድርጎን ሲናገር፤ የኢየሱስን ቃል ሰምቶ የማይፈጽመውን ሰው ደግሞ ቤቱን ያለመሰረት በአፈር ላይ ዝም ብሎ የሚያስቀምጠውን ሰው እንደሚመስል ሲነግረን፤ ውጤቱም ጎርፍና የውሃ ሙላት በመጣ ጊዜ ይታያል ማለት ነው።

# ጥናት አሥራ ሁለት ሉቃስ 7:1-50 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ የመቶ አለቃ አገልጋዩን እጅግ ይወደው እንደነበረ ቁ2ትን መመልከት እንችላለን። ይህ ሰው ወደ ኢየሱስ ለመቅረብ የተጠቀመበት መንገድ የአይሁድ ሽማግሌዎችን ወደ እርሱ በመላክ ነበረ። የተላኩት ሰዎች ይህ የመቶ አለቃ ከኢየሱስ እርዳታን መቀበል ይገባዋል ብለው ያመኑና የደመደሙበት ምክንያት፤ በአንደኛ ደረጃ ይህ ሰው የእስራኤልን ህዝብ የሚወድ ነው፤ ሁለተኛ ደግሞ ምኩራባቸውንም ያሰራላቸው እርሱ ነው።
2. ይህ ሰው በቁ6 ላይ እንደምንመለከተው ራሱን ከኢየሱስ ጋራ ሲያስተያይ እጅግ ዝቅ ያለ እንደሆነ፤ እንዲሁም ደግሞ ኢየሱስን እጅግ ትልቅ በሆነ ሥፍራ ላይ ከፍ አድርጎ ሲያስቀምጥ፤ እርሱ ደግሞ በኢየሱስ ፊት መቅረብ የሚገባው ሰው እንዳልሆነ ራሱን ይቆጥራል። የተጠቀመበት ምሳሌ አዛዥና ታዛዥ በመጠቀም ሲሆን፤ ይህም ማለት ኢየሱስ በሁሉም ነገር ላይ አለቃና ባለስልጣን ስለሆነ ማድረግ የሚያስፈልገው መናገር ብቻ እንደሆነ አምኗል። የመቶ አለቃው የተናገረው ሁሉ ነገር አስገራሚ ነገር ቢሆንም፤ እኔ እንደምረዳው ኢየሱስን ያስገረመው ዋነኛ ነገር የመቶ አለቃው ስለ እግዚአብሄር የማያውቅና ከእስራኤል ወገን አለመሆኑ ይመስለኛል።
3. በአንደኛው ውስጥ ተአምር ያስፈለገው ባለሥልጣን ሲሆን፣ በሌላው ግን ምንም የሌላት መበለት ነች፤ በመጀመሪያው ታሪክ ፈውሱ የተከናወነው በመቶ አለቃው ጥያቄ ሲሆን፣ በሁለተኛው ግን መነሻው በኢየሱስ ርህራሄ ነው፤ የመጀመሪያው የሞተ ሰው ሳይሆን የታመመ ነው፣ ሁለተኛው ግን የሞተ ሰው ነው፤ የመጀመሪያው የታመመበት ባሪያው ሲሆን፣ በሁለተኛው ግን አንድ ልጇ ነበረ፣ በመጀመሪያው ታላቅ እምነት እናያለን፣ በሁለተኛው ላይ ስለ እምነት የተነገረም ነገር አናይም። በህብረተሰብ ውስጥ ያለን ሥፍራ ምንም ዓይነት ሚና የለውም እላለሁ፤ ምክንያቱም መቶ አለቃውንም ሆነ፤ መበለቲቱን እኩል ነው ጌታ የተቀበላቸው።
4. ለእግዚአብሄር ምስጋና አምጥቷል፣ ታላቅ ነብይ በመካከላቸው እንደተነሳ እንዲገነዘቡ ረድቷቸዋል፣ እግዚአብሄር ህዝቡን እንደጎበኘ መረዳት ችለዋል፣ በመጨረሻም የኢየሱስ ዝና በመላው ይሁዳና ባካባቢው ባለው አገር ሁሉ እንዲወጣ አድርጓል። ለዚህች መበለት ሴት አብዛኛው የከተማው ህዝብ እንዳዘነና ቢችል ሁኔታዋን ሊቀይርላት ቢችል የሚወድ እንደሚሆን አያጠራጥርም፤ ነገር ግን የሴትየዋን ሁኔታ ለመቀየር የኢየሱስ በስፍራው መገኘት ግድ ነበረ።
5. በተለይ የማቴ 11፡2-6 ያለው ክፍል እንደሚጠቁመን ዮሐንስን ወደዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ያደረሰው እኔ እንደሚመስለኝ በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ ምናልባትም ኢየሱስ እርሱ መሲሁ ከሆነና ይህንን ሁሉ ተአምራት ማድረግ ከቻለ እኔንም ማውጣት ነበረበት የሚለው አስተሳሰብ ሳይሆን አይቀርም እላለሁ። ለሰዎቹ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት፤ እውነትን ለመቀበል ዝግጁ ስላልሆናችሁ በምንም መንገድ እናንተን ማስደሰትና እውነቱን እንድትቀበሉ ማድረግ አይቻልም፤ ሃዘንም ሆነ ደስታ አይስማማችሁም ነው የሚላቸው።
6. ከኢየሱስ ድርጊት የምንማረው፤ የኢየሱስ ማንኛቸውንም አይነት ሁኔታዎች በመጠቀም እውነትን ለማስተማር እንደሚጠቀም እንጂ፤ ከነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋራ መታየትም አልፈልግም የሚለውን አስተሳሰብ እንደማያስተናግድ እናያለን።
7. ስለዚህች ሴት ማንነት በዚህ ክፍል የተነገረው ነገር፤ ይህች ሴት ፈረሳዊው ይኖርበት በነበረው ከተማ ውስጥ የምትኖር ሃጥያተኛ ሴት እንደነበረች እናነባለን። ሽቶ ይዛ መጣች፣ እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ አራሰች፣ በፀጉሯ እግሩን አበሰች፣ እግሩን እየሳመች ሽቶ ቀባችው።
8. ይህ አነጋገር ትክክለኛ አይደለም፤ ምክንያቱም ፈሪሳዊው ሴትየዋ ያደረገችውን ሁሉ ተመልክቶ ምንም የተናገረው ነገር አናይም፤ ሆኖም ቁ39 እንደሚነግረን "በልቡ አሰበ" ነው የሚለው። ስምዖን ምንም ቃል ከአንደበቱ ሳያወጣ ከኢየሱስ መልስ ማግኘቱ የኢየሱስን አምላክነት ያረጋግጣል። በዚያ ሥፍራ የተካሄደው ነገር ለስምዖን ያረጋገጠለት ነገር ኢየሱስ ነብይ ነው የሚባለው ነገር እውነት አለመሆኑን ነበረ።
9. በዚህ ክፍል የፍቅር መግለጫ ሆኖ የቀረበው ነገር ለኢየሱስ ያደረጉት ነገር ነው።

# ጥናት አሥራ ሶስት ሉቃስ 8፡1-56 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ፣ አሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት፣ መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣ ሶስና፣ ሌሎች ብዙዎች ከርኩሳን መናፍስትና ከደዌ የተፈወሱ ሴቶች፣ ብዙ ህዝብ፣ እንዲሁም ከተለያዩ ከተሞች የጎረፉ ሰዎች ይገኙበታል። ኢየሱስን ይሰሙት የነበሩት ሰዎች ቁጥር በጣም ብዙ እንደነበረ የሚጠቁሙን፤ ቁ3 ስለ ሴቶቹ ሲናገር "ብዙዎች " ቁ4 "ብዙ ህዝብ" እና እንደገናም ቁ4 "ወደ እርሱ በሚጎርፉበት ጊዜ" የከሚሉት አነጋገሮች የሰሚዎቹ ቁጥር እጅግ ብዙ እንደነበረ ይጠቁሙናል።
2. ቃሉን የሚሰሙትን ሰዎች በአራት አይነት ነው ከፍሏቸው የምናየው። በነዚህ አራት አይነት ሰዎች ሁሉ ውስጥ የምናየው አንድ የጋራ የሆነ ነገር ቢኖር፤ ሁሉም ቃሉን ይሰማሉ (ቁ12፣ 13፣ 14፣ 15)። በእኔ አመለካከት እነዚህ አራት አይነት ሰሚዎች ሁሉ የተዘራባቸው ወይም የሰሙት አንድ አይነት ቃል ሲሆን፤ ልዩነት ያመጣው ነገር ቃሉ የተዘራበት መሬት ዓይነት፣ ማለትም ልባቸው እንደሆነ በተለይ በቁ15 ላይ ከምናየው ስለ አራተኛው ሰው ከተነገረው እንረዳለን።
3. ይህ ክፍል ትክክለኛ ቁጥሩን አይናገርም፤ ሆኖም ከአንድ በላይ እንደሆነ "ወንድሞችህ" ከሚለው አነጋገር እንረዳለን። ጌታ ይህንን መናገሩ ቤተሰባችሁ አስፈላጊ አይደለም የሚለውን አመለካከት ለመጠቆም አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ ከሆነ በ1ኛ ጢሞ 5፡8 ላይ ከተነገረው ሃሳብ ጋራ የሚጋጭ ይሆናልና ነው፤ የኢየሱስ ሊያስተምራቸው የፈለገው እውነት የእግዚአብሄርን ቃል ሰምቶ መታዘዝ ምን ያህል ትልቅ ሥፍራ እንዳለውና ለዘለዓለሙ የእግዚአብሄር ቤተሰብ እንደሚያደርግ ለማስረዳት ነው።
4. አንደኛው በቁ25 ላይ የሚገኘውና ኢየሱስ የጠየቀው "እምነታችሁ የት አለ?" የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው በዚያው በቁ25 ላይ የሚገኝ ደቀ መዛሙርቱ የጠየቁት "ይህ ነፋስንና ውሃን የሚያዝ፣ እነርሱም የሚታዘዙለት ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?" የሚል ነው። ደቀ መዛሙርቱ በ ፍርሃትና በመደነቅ የሞላቸው ኢየሱስ ማዘዝ መቻሉ አይደለም፤ ምክንያቱም ማንም ሰው ተነስቶ ለማዘዝ የሚከለክለው አይኖርም፤ ደቀ መዛሙርቱን ያስደነቀውና ጥያቄ ውስጥ የጨመራቸው የነፋሱና የውሃው ለኢየሱስ ትዕዛዝ መታዘዛቸው ነው።
5. ይኖር የነበረው በጌርጌሴኖን እንደነበረ ይነግረናል፣ ለብዙ ጊዜ ልብስ አይለብስም ነበር፣ የሚኖረው በመቃብር ቦታ ነበረ፣ ርኩስ መንፈስ በየጊዜው ይነሳበት ነበረ፣ በሰንሰለትና በእግር ብረት ይታሰር ነበረ፣ ሰንሰለቱን ይበጣጥስ ነበረ፣ ጋኔኑ ወደ በረሃ ይነዳው ነበረ። በዚህ ክፍ በተለይም በቁ28 ላይ ኢጋንንት የያዘው ሰው የሚናገረው ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ሲሆን፤ ነገር ግን ይህ ማለት ለደህንነቱ የሚሆን አይነት እውቀት ሳይሆን፤ ያዕቆብ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ቁ19 ላይ ኢጋንንት እንደሚያምኑና እንደሚንቀጠቀጡ የተናገረው አይነት ደህንነት የማይገኝበት አይነት እውቀት ነው።
6. በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ከሰይጣን የበላይ መሆኑን የሚያሳየን አንዱ ክፍል በቁ31 እና በቁ32 ላይ የምናያቸው አንድን ነገር ለማድረግ ኢየሱስን ማስፈቀድ እንደነበረባቸው የሚናገረው ክፍል ግልጽ ይመስለኛል። የጌርጌሴኖን ሰዎች በሰውየው ህይወት ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ ታላቅ ፍርሃት እንዳደረባቸው፤ ስለዚህም ኢየሱስን ከከተማቸው ወጥቶ እንዲሄድላቸው እንደለመኑት እናነባለን። ከዚህ ልንማር የምንችለው፤ ኢየሱስ እኛ በህይወታችን ካልፈለግነውና ሥፍራ ካልሰጠነው አስገድዶ የሚገባ እንዳልሆነ ያስተምረናል።
7. ቁ37 ላይ ስንመለከት የጌርጌሴኖን ሰዎች ኢየሱስን ከከተማቸው እንዲወጣላቸው ሲለምኑት፤ በዚህ ሥፍራ ደግሞ ቁ40 ላይ ኢየሱስ ወደ ከተማቸው በመምጣቱ ህዝቡ በደስታ እንደተቀበሉት ማለትም በሁለቱ መሃል ተቃራኒ የሆነ አቀባበልን እንመለከታለን። "አንድ ሰው ነካኝ" የሚለው አነጋገር ለጴጥሮስ፣ ቢዚህ ሁሉ ግፊያ ውስጥ አንድ ሰው ብቻ ሊነካ አይችልም፣ ብዙ ሰዎች ናቸው የነኩህ የሚል አስተሳሰብ ሲኖረው፤ ኢየሱስ ግን "መንካት" የሚለው የሚጋፋውን ሰው ሁሉ ሳይሆን ቁ47 እንደምናየው በአላማና በእምነት፣ አንድን ነገር ከኢየሱስ በመጠበቅ የሚደረገውን አይነት መንካት ነው።
8. በሰው አመለካከት መልካም አልነበረም የሚያሰኘው ኢየሱስ ለልጁ በጊዜው እንዳይደርስላት አስረፈደችው ማለት ሲቻል፤ መልካም ነበረ የሚያሰኘው ደግሞ እሷ ከበሽታዋ ወዲያው ስትፈወስ በአይኑ ማየቱ እምነቱን ይጨምርለታል።

# ጥናት አሥራ አራት ሉቃስ 9፡1-62 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት እንዲሄዱ ሲልካቸው የሰጣቸው ሁለት ነገሮች፤ አንዱ ተልዕኮ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሥልጣን እንደሆነ መመልከት ይቻላል። እነዚህን ስድስት ቁጥሮች ብቻ በመመልከት የሐዋርያቱ ዋነኛ ተልዕኮዎች ናቸው ማለት የሚቻሉት፡ አጋንንትን ሁሉ ማውጣት (ቁ1)፣ ደዌን መፈወስ (ቁ1)፣ የእግዚአብሄርን መንግሥት መስበክ (ቁ2) እና የታመሙትን መፈወስ (ቁ2) ናቸው።
2. ኢየሱስ በዚህ ቦታ በአገልግሎት ደክመው የመጡትን ሐዋርያቱንና እራሱን ጨምሮ ለብቻቸው ማረፍና ጊዜ መውሰድ እንደፈለገ ይመስለኛል። ኢየሱስ ያሰበውን ዓይነት የእረፍት ጊዜ ለማግኘት ያልቻለበት ምክንያት ህዝቡ እርሱ በሄደበት ሁሉ ስለሚከተሉት ለብቻቸው ለመሆን አልቻሉም። ጌታ የሱስ ምንም እንኳን ለራሱና ለሐዋርያቱ ያቀደው ነገር እረፍት ቢሆንም የህዝቡን ረሃብና ፍላጎት ተመልክቶ በድካምም ቢሆን እንዳገለገላቸው ሁሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ማረፍ በሚኖርብን ሰዓት እንኳን የሰዎችን መንፈሳዊ ረሃብ ለማገልገል የራሳችንን ፍላጎት መስዋዕት ማድረግ እንደሚኖርብን እንማራለን።
3. ለደቀ መዛሙርቱ ያቀረበላቸው ሁለት ጥያቄዎች፡ የመጀመሪያው ህዝቡ እኔን ማነው ይሉኛል? ሁለተኛው ደግሞ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? የሚሉ ነበሩ። በከተማው ስለእርሱ የሚወራውን ነገር ለመስማት ሳይሆን እያስተማራቸውና አብረውት እየተጓዙ ያሉት ደቀመዛሙርቱ ማንነቱን ተረድተው እንደሆነ ለማወቅ ይመስለኛል። “እናንተስ ማነው ትሉኛላችሁ?” የሚለው ወሳኝ ነው እላለሁ፤ ምክንያቱም ህይወታቸውን ሰጥተው እየተከተሉት ያሉትን ሰው ላይ ማንነት ማወቃቸው ለዘላለም ህይወት ስለሚያበቃቸው ነው።
4. ኢየሱስ የሚያልፍባቸው አራት ነገሮች፡ 1) ብዙ መከራ መቀበል፣ 2) መናቅ፣ 3) መገደልና፣ 4) ከሙታን መነሳት ናቸው። እነዚህን በተለይም ሶስቱን ነገሮች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ምክንያት የሚሆኑት፤ ሽማግሌዎች፣ ካህናት፣ አለቆችና ጻህፍት የሚባሉት ሰዎች ናቸው። ቀደም ብሎ ቁ22ን ስናይ በራሱ ላይ ሊደርሱ ያሉትን ነገሮች ገልጾ የነገረ ሲሆን፤ በዚህ በቁ23-27 ደግሞ ደቀመዝሙር ከመምህሩ ስለማይበልጥ እርሱን እከተላለሁ የሚል ሰው ህይወቱ ራሱን መካድና መስቀል መሸከም እንደሚኖርበት አውቆ እንዲገባ ያስጠነቅቃል።
5. ኢየሱስ ሶስቱን ደቀመዛሙርቱን ይዞ ወደ ተራራ የወጣበት ምክንያት ለጸሎት ነበረ። እርሱ ተግቶ በሚጸልይበትና የተለየ ልምምድ ውስጥ ገብቶ በነበረበት ሰዓት፤ ከእርሱ ጋራ ይዟቸው ያመጣቸው ሶስቱ ግን እንቅልፍ ተጭኗቸው ተኝተው እንደነበረ ቁ32 በግልጽ ይነግረናል። ከዚህ መማር የምንችለው ነገር፣ መንፈሳዊ ህይወት ደስ የሚያሰኙና ቢቀጥሉ የምንመርጣቸው ዓይነቶች የተራራ ልምምዶች ያሉበት ቢሆንም እንኳን፤ በተራራው ላይ የተሞላነውን ሃይል በእስራት ያሉትን ለማገልገል ከተራራው ሥር ላሉት ሰዎች እንደምናስፈልግ ያስታውሰናል።
6. ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስን መሞት በልባቸው እንዲያኖሩት የሚፈልግበት ምክንያት፤ እያደረገ ያለውን ተአምራት እየተመለከቱና ኢየሱስ ደግሞ ምድራዊ መንግሥትን መስርቶ ንጉስ ይሆናል የሚለው አመለካከት ስለነበረ ይህንን ከአምሯቸው በማውጣት ልባቸውን ለሚመጣው ነገር ለማዘጋጀት ነው። በዚህ ክፍል ያለውን ደቀመዛሙርቱ የተነገራቸውንና የሚሆኑትን ስንመለከት፤ ሰዎቹ መንፈሳዊ ነገር ገና ያልገባቸውና ኢየሱስ የሚነግራቸው ውስጣቸው እንዳልገባ እንረዳለን።
7. በነዚህ ደቀመዛሙርት መሃል የጊዜው ጥያቄና መወያያ የነበረው ርዕስ፣ ከመካከላችን ታላቅ ወይም የሚበልጠው ማን ነው? የሚለው ነገር ነበረ። ለዚህ ሃሳብ የኢየሱስ አጭር መልስ ሆኖ የቀረበው በቁ48 ላይ የተናገረው “ከሁላችሁ የሚያንስ እርሱ ከሁሉ ይበልጣል” የሚል ነው። በዮሐንስ አመለካከት አንድ ሰው አጋንንትን ለማስወጣት ወይም ተአምራትን ለማድረግ የእነርሱ ግሩፕ ውስጥ መሆን ይጠበቅበታል።
8. ሰውየው ኢየሱስን ለመከተል ፈቃደኛነቱን ለማረጋገጥ የተናገረው ነገር፤ ወደሚሄድበት ሁሉ እንደሚከተለው በመናገር ነው። ኢየሱስ ግን ያ ብቻ በቂ እንዳልሆነና እርሱን ከተከተለ ያለውን ሁሉ ትቶ የእምነት ኑሮ ለመኖር መወሰን እንዳለበት ነው የነገረው። ሁለቱ ሰዎች ምክንያታቸው የሚመሳሰለው፤ አስቀድመው ማድረግ ያለባቸው ነገር እንዳለ ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን አልተቀበለውም።
9. ልጁ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት መንገድ ሲጀምር ቀድሞ ያሰቃየው የነበረው መንፈስ ጥሎ ማንፈራገጥ ጀመረ። በእኔ አስተያየት ይህ የተከሰተው ሁኔታ ኢየሱስ አንድ ነገር ሊያደርግልኝ ይችላል ብሎ በእምነት ልጁን ይዞ የመጣው ሰው ይህንን በማየት በልቡ ተስፋ የመቁረጥ ነገር ሊገባበት እንደሚችል ስገምት፤ የሰይጣንም አላማው ይኸው ይመስለኛል።

# ጥናት አሥራ አምስት ሉቃስ 10፡1-42 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህን ሰዎች ጌታ እንዲያደርጉ የሚነግራቸው ሁለት ነገሮች፤ አንደኛው እግዚአብሄር ሰራተኞችን ወደ መከሩ እንዲልክ መለመን ወይም መጸለይ (ቁ2) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ወደ መከሩ መሄድ ነው (ቁ3)። እነዚህ ሶስት ነገሮች ስለተልኳቸው የሚያንጸባሩቁት ሶስት ሃሳቦች፡ እንደ በጎች በተኩላ መሃል መላክ የተልዕኮውን አደገኛነት ሲያንጸባርቅ፣ ኮረጆና ከረጢት አለመያዝ ተልዕኮው በእምነት የሚሰራ እንደሆነና፣ በመንገድ ለሚያገኙት ሰላምታ አለመስጠት ደግሞ የተልዕኮውን አስቸኳይነት የሚጠቁሙ ሃሳቦች ናቸው።
2. የኢየሱስን ተልዕኮው ተቀብለው የሚሄዱት ሰዎች ሊገጥሟቸው የሚችሉ ሁለት አይነት ሰዎች እንደሆኑና፤ እነዚህም ደግሞ አንደኛዎቹ በቁ8 ላይ የምናያቸውና የሚቀበሏቸው ሰዎች ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ ግን በቁ10 የምናያቸው የማይቀበሏቸው ሰዎች ናቸው። መልዕክተኞቹን ለተቀበሏቸውም(ቁ9) ላልተቀበሏቸውም(ቁ11) ኢየሱስ ለሁሉም እንዲደርስ የፈለገው መልዕክት “የእግዚአብሄር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች” የሚል ነበረ።
3. ደቀ መዛሙርቱ የወንጌልን መልዕክት ሲናገሩና ሰዎች ሰሟቸው ወይም አልሰሟቸውም ማለት፤ ኢየሱስ ተናግሯቸው እንደሰሙት ወይም እንዳልሰሙት ሆኖ እንደሚቆጠርና ልዩነት እንደሌለው፤ እንዲያውም ያ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን የላከውን አብንም እንደሚሰሙ ወይም እንደማይሰሙ ይቆጠራል። እነርሱ ደስታቸው በሰሩት ነገር ላይ ሲሆን ኢየሱስ ግን የተሰራላቸው ነገር እንደሚበልጥና በዚያ ይበልጥ እንዲደሰቱ አቅጣጫውን ያመለከታቸዋል።
4. ኢየሱስን ሃሴት እንዲያደርግ ያደረገው ነገር የደህንነት ሚስጢር ወይም የእግዚአብሄር መንግሥት ነገር ከጥበበኞችና ከአዋቂዎች ተሰውሮ እንደ ህጻናት በሞኝነት መቀበል ለሚፈልጉት እንዲገለጥ የእግዚአብሄር ፈቃድ በመሆኑ ነው። ነብያቱም ሆኑ ነገሥታት የመሲሁን የኢየሱስን መምጣት በመጠባበቅ ሊያዩት ይናፍቁ እንደነበረ፤ ነገር ግን የማየት እድል እንዳልገጠማቸው፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን እርሱን የማየት እድል ስለገጠማቸው እድለኞች መሆናቸውን ሲናገር ነው።
5. ይህ ሰው ለኢየሱስ ያቀረበለት ጥያቄ “መምህር ሆይ፤ የእግዚአብሄርን መንግሥት ለመውረስ ምን ላድርግ?” የሚል ነበረ። ሰውየው ጥልቅ የሆነ የህግ እውቀት ያለው ሰው እንደሆነ ክፍሉ የሚናገር ሲሆን፤ ይህ ሰው ግን በእግዚአብሄር ቃል ላይ የነበረውን እውቀት ለተንኮልና ኢየሱስን ለመፈተን ሲጠቀምበት ነው የሚታየው።
6. ኢየሱስ የህግ አዋቂውን ጥያቄ መልሶ ሌላ ጥያቄ ራሱን በመጠየቅ ጥያቄን በጥያቄ ነው የመለሰው። ይህ ሰው ወረድ ብለን በቁ29 ላይ ስንመለከተው ጽድቅን ከእግዚአብሄር ለመቀበል የመጣ ሰው እንዳልነበረና ጽድቅን በራሱ ለማምጣት የሚሞክር ሰው እንደነበረ ገልጾ ያሳየናል። በቁ29 ላይ ኢየሱስን የጠየቀው ሁለተኛ ጥያቄ “ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?” የሚል ነው።
7. ኢየሱስ ለሁለተኛውም ጥያቄው ቀጥተኛ መልስ አልሰጠውም። እኔ እንደሚመስለኝ ለዚህ ህግ አዋቂ ኢየሱስ ቀጥተኛ መልስ መስጠት ያልፈለገው፤ በመጀመሪያም አመጣጡ ለፈተና እንጂ ለመማር ስላልሆነ የሚያውቀውን ነገር ኢየሱስ ደግሞ ሊነግረው አላስፈለገውም፤ ነገር ግን ከሰውየው ከራሱ ውስጥ መልሱን ማውጣት ስለነበረበት ነው። እኔ አይመስለኝም፤ ምክንያቱም ሰውየው የጠየቀው ለእርሱ ጓደኛ የሚሆነውን ሰው ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን የመለሰለት እርሱ ለሌሎች በጎ በማድረግ ጓደኛ መሆን እንደሚችል ነው።
8. ኢየሱስ በነማርታ ቤት ውስጥ ተገኝቶ ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር የእግዚአብሄርን ቃል ሲያካፍል ነው።

# <u>ጥናት አሥራ ስድስት ሉቃስ 11፡1-54 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ጳውሎስ በተሰሎንቄ ውስጥ ሳናቋርጥ እንድንጸል መናገሩ ተንበርክከን እንድንውል ማለቱ እንደሆነ ከኢየሱስ የፀሎት ህይወት ተመልክተናል። ጳውሎስ ለማለት የፈለገው ዘወትር ህይወታችን ከእግዚአብሄር ጋራ የተቃኘ እንዲሆን፤ ኑሯችንንና አስተሳሰባችን ዘወትር ልክ በፀሎት ላይ እንዳለ ሰው እንዲሆን ማለት ይመስለኛል። ስለፀሎት ፍላጎቱ የተነሳው መሪው የነበረው ኢየሱስ ራሱ ሲፀልይ ስለተመለከተ ነበረ። ከዚህ የምንማረው ሰዎች አንድን ነገር ለማድረግ የሚነሳሱት መሪዎቻቸው ሲያስተምሯቸው ብቻ ሳይሆን፤ ያስተማሯቸውን ነገር በተግባር ራሳቸው ሲያሳዩት እንደሆነ መማር እንችላለን።
2. ደቀመዝሙሩን ፀሎት ለማስተማር የተጠቀመባቸው ሁለት የግንኙነት ዓይነቶች፤ በሁለት ጓደኞች መሃልና በአባትና በልጅ መሃል ያለውን ግንኙነት ነው ሲጠቀም የምናየው። ጌታ በነዚህ ምሳሌዎች ተጠቅሞ ሊያስተላልፍ የፈለጋቸው ሁለት ሃሳቦች፡ አንደኛው መፀለይ መልስን እንደሚያስገኝ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚአብሄር መልካምን ነገር ለምኖ ክፉን ነገር መቀበል የሚል ነገር እንደማይኖር ነው።
3. አንደኛዎቹ ምናልባትም አብዛኛዎቹ ሰዎች በተደረገው ተአምራት የተገሙ እንደሆነ ቁ1 ይነግረናል፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ አጋንንትን የሚያስወጣው በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል ነው የሚሉ ሲሆኑ፤ ሶስተኛዎቹ ሃይሉን ሊፈታተኑት ተጨማሪ ተአምራት እንዲያሳያቸው የሚጠይቁ ነበሩ። ኢየሱስ በዚህ ክፍል ምላሽ ሲሰጥ የምንመለከተው በአጋንንት አለቃ በብኤል ዜቡል አጋንንትን ያወጣል ብለው ለሚሉት ሰዎች ነው።
4. ከቁ14 ጀምሮ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተነገረው ኢየሱስ አጋንንቱን ማስወጣቱ አጠያያቂ ስለሆነባቸው በቁ21-22 ላይ የሚነግራቸው ሰይጣን ምንም ዓይነት ብርቱና ንብረቱን ለመከላከል ቢሞክር እንኳን፤ ከእርሱ ይልቅ ብርቱ የሆነው ኢየሱስ ሲመጣ ግን ትጥቁን መፍታት ግድ እንደሚሆንበት የሚያስተምር ክፍል ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ ጌታችን እየተናገረ ያለው ነገር ያነጣጠረው በቁ1 ላይ ከአጋንንት እስራት በተፈታው ሰው ላይ እንደሆነ አያጠራጥርም።
5. የእነዚህን ሰዎች ወይም የትውልዱን ምልክትን መፈለግ ኢየሱስ በጥሩ መልኩ ሳይሆን የተመለከተው መልካም ነገረ እንዳልሆነ ነው ሊነግራቸው የሞከረው። ዮናስ በዓሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀን ቆይቶ መውጣቱ ተአምራት እንደነበረ፤ ኢየሱስም በምድረ ከርስ ወይም በመቃብር ውስጥ ሶስት ቀናት አድሮ በትንሳኤ መውጣቱ ለትውልዱ በቂ የሆነ ምልክት መሆን እንዳለበትና ከዚያ በላይ ምልክትም እንደማይሰጣቸው ነው የሚነግራቸው።
6. መብራትን አብርቶ ከእንቅብ በታች ማስቀመጥ ጤናማነት እንዳልሆነ፤ የአይናችን መኖር ለሰውነታችን ክፍሎች ጠቃሚ የሚሆነው ብርሃን እስካለው ድረስ እንጂ ጨለማ ከሆነ ጥቅም እንደሌለው ሁሉ፤ በእኛ ውስጥ የበራው የክርስቶስ ብርሃንም ለሌሎች የማብራትና ጨለማቸውን የመግፈፍ ስራውን መስራት አለበት። ኢየሱስ ለፈሪሳዊው ሊያስተምረው የፈለገው እውነት፤ ዋነኛ መጽዳት የሚኖርበት የሰው ውስጡ ሲሆን፤ እግዚአብሄር ውስጥንም ውጭንም ስለፈጠረ ሁለቱንም ማጽዳትም መልካም እንደሆነ አስተማረው።
7. ፈሪሳውያኑ ከተለያዩ ከሚያገኟቸው ነገሮች ሁሉ ለእግዚአብሄር የሚሆነውን ይሰጣሉ፤ ሆኖም ግን ያላቸውን ከመስጠት አልፈው ራሳቸው እንደማይሰጡ፤ ወይም ደግሞ ለፍትህና እግዚአብሄርን ለመውደድና ለማምለክ እንደማይሰጡ ይነግራቸዋል። እነኚህን ሁሉ ኢየሱስ የዘለፋቸውን ሃሳቦች በአንድ ቃል ብናገር “ግብዞች” የሚለውን ቃል እመርጣለሁ።
8. ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ ፈሪሳውያኑ፣ ስለ ፃህፍትና፣ ስለህግ አዋቂዎቹ የተናገራቸው ነገሮች አንድም ሳይቀር ትክክል እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፤ የሰው ባህር ግን ስለራሱ እውነትን ከመስማት ይልቅ የሚስማማውንና ውሸትም እንኳን ቢሆን በለበጣና በመሸፋፈን ቢነገርለት ስለሚወድ፤ የኢየሱስ ግልጽነት በጭራሽ ስለማይስማማቸው ነው ተቃውሚቸው እየጠነከረ የመጣው።

# ጥናት አሥራ ሰባት ሉቃስ 12፡1-59 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ የተናገረው የማስጠንቀቂያ ቃል “ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠንቀቁ፤ ይህም ግብዝነት ነው” የሚል ነበረ። በቁ1 ላይ የፈሪሳውያንን ግብዝነት አስመልክቶ የተናገረ ሲሆን፤ ቀጥሎ የተናገራቸው ሃሳቦች ምንም እንኳን ፈሪሳውያን የሆኑትን እውነተኛ ማንነታቸውን ሰውረው ሌላ መልክ ቢያሳዩም፤ እውነተኛ ማንነታቸው ተገልጦ የሚታይበት ጊዜ እንደሚመጣ ለማሳየት ነው። ሰው ሊገድል የሚችለው ሥጋን ብቻ ስለሆነ፤ ነገር ግን እግዚአብሄር ሥጋንም ገሎ ወደ ገሃነም መጣል ሙብት ስላለው ነው ይለናል።
2. ሰዎች ይዘው ወደ ምኩራብ፣ ወደ ገዥዎችና ባለሥልጣናት ስለሚያቀርቡበት ምክንያት፤ በቁ8 እና 9 ላይ “በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ…” እያለ የሚናገረው ሃሳብ፤ ሰዎች ስለክርስቶስ በሚመሰክሩበት ጊዜ ሊደርስባቸው የሚችለው ነገር ነው። ለሰውየው እርሱ በእነርሱ መሃል ፈራጅ እንዳልሆነ ከተናገር በኋላ ለህዝቡ የተናገረው ሃሳብ፤ በእኔ አመለካከት ዋነኛ ትምህርት ነው ብዬ የምወስደው ፡ የሰው የህይወቱ ምንነት የሚለካው ባለው የገንዘብ መጠን እለመሆኑን ነው ማስተማር የፈለገው።
3. “እንዲህ አደርጋለሁ”፣ “ያሉኝን ጎተራዎች አፈርስና”፣ “ሰፋ ያሉ ጎተራዎች እሰራለሁ”፣ “ምርቴንና ንብረቴን ሁሉ አከማቻለሁ”፣ “እረፊ፣ ብይ፣ ጠጪ፣ ደስም ይበልሽ እላታለሁ” እና የመሳሰሉት አነጋገሮቹ በዚህ ሰው እቅድ ውስጥ እግዚአብሄር ጭራሹን እንደሌለ እናያለን። በእኔ አመለከከት ይህንን ሰው ሞኝ ያሰኘው ነገር፤ ነገን በእጁ እንደያዘ ሰው ሆኖ መናገሩና፤ እስትንፋሱን በእጁ የያዘው እግዚአብሄር መሆኑን መርሳቱ ይመስለኛል። እግዚአብሄርን ያልጨመረና ራስ ተኮር የሆነ ሃብታምነት ከንቱ መሆኑን ሊያስተምራቸው ነው።
4. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ደቀመዛሙርቱን እያወዳደረ ለማስተማር የተጠቀመባቸው ሁለት ነገሮች፤ ወፎችና አበቦች ናቸው። ህይወት ከምግብ ሰውነት ደግሞ ከልብስ የሚበልጥ ከሆነ፤ ህይወትንም ሆነ ሰውነትን የሰጠን እርሱ እግዚአብሄር መሆኑ፤ የሚበልጡትን ነገሮች ሊሰጠን የቻለ እግዚአብሄር ያነሱትን ነገሮችም ሊሰጠን እንደሚችል ልናምነው እንደሚገባን ለማስተማር ነው።
5. በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ለእኛ በተለይ ቁጥር 30ን ስናነብ አባታችን እንደሆነ አድርጎ ነው የሚነግረን። እኛን አማኞችን ካላመኑት ሰዎች የተለየን ሆነን መገኘት እንደሚኖርብን የሚጠቁን ክፍል ቁ30 ላይ የምናነበው አነጋገር ነው፤ ከአህዛብ የተለየ ሆነን መገኘት የሚጠበቅብንም፤ ቁ31 ላይ እንደምናየው እኛ ልባችን ሊሆን የሚገባው በእግዚአብሄር መንግሥት ነገር ላይ ሆኖ፤ ለምድራዊው ኑሯችንም እግዚአብሄርን መተማመን እንደሆነ ነው።
6. በ38-45 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄርን በተለያየ መልኩና በተለያዩ ምሳሌዎች በማስረዳት ከእኛ ጋራ ያለውን ግንኙነት በጌታነት ሲስልልን ነው የምንመለከተው። እነዚህን ሁለት አገልጋዮች፤ የጌታውን ፈቃድ እያወቀ የሚያጠፋና፣ የጌታውን ፈቃድ ሳያውቅ የሚያጠፋ ብለን መጥራት እንችላለን። የነዚህ ሰዎች የቅጣታቸው ልዩነት፤ እያወቀ ያጠፋው ከፉኛ ሲገረፍ፣ ሳያውቅ ያጠፋው ግን በትንሹ እንደሚገረፍ እናነባለን።
7. በሉቃስ 12 ላይ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ሲል፤ ከቤተ ሰብ መሃል አንዱ ክርስቶስን አምኖ ለመከተል በሚጀምርበት ጊዜ በሌሎቹ የቤተሰብ አካላት ውስጥ ለዚያ ሰው የሚኖራቸውን አመለካከት ሳያውቁት ወደ ጥላቻ እንደሚመጡ ለማስረዳት ሲሆን፤ በዮሐንስ 14 ላይ ግን በእርሱ ላመኑት ሰዎች የሚሰጠውን የሰላም ዓይነት ሲናገር ስለሆነ ሁለቱ ሃሳቦች የተለያየ ነገር ላይ ያተኮሩ ናቸው።
8. ኢየሱስ ህዝቡን የሚያበረታታው የሰማዩንና የምድሩን መልክ ተመልክተው ሊመጣ ያለውን መለየት እንደሚችሉ ሁሉ፤ ያሉበትን ዘመን መመርመር እንዲችሉ ነው። እኛንም ቢሆን በዚህ ቃሉ የሚያበረታታን አይኖቻችንን ከፍተን በአካባቢያችን የሚካሄደውን ሁኔታ በማጤን መመልከት የጌታችንን ዳግም ምጻት መቅረቡን በቀላሉ መረዳት ከብዙ ዓይነት ውዥንብር እንደምንጠበቅ ነው።

<u>ጥናት አሥራ ስምንት ሉቃስ 13፡1-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ኢየሱስ ከሰዎቹ ከሰማው ዜና በተጨማሪ የሚያውቀው ሌላ ወሬ በቁ4 ላይ የምናነበው በሰሊሆም ግንብ ተንዶባቸው ስለሞቱት ሰዎችም ያውቅ ነበረ። እነዚህ ሰዎች ያመጡለትን ዜና ኢየሱስ ሲጠቀምበት የምናየው፤ ለነዚያው ዜናውን ላመጡት ስዎችና ለሰሚዎቹ ሁሉ የሚሆን የራሳቸውን ህይወት ሊያዩ የሚችሉበትን መንፈሳዊ ሃሳብ በማውጣት የማስተማሪያ መንገድ አድርጎ ሲጠቀምበት ነው የምንመለከተው። በማናቸውም በአካባቢያችን የምናያቸው ሁኔታዎች ለራሳችን መማሪያ ሊሆኑን እንደሚችሉ መማር እንችላለን።
2. እነዚህ ሁለት ክፍሎች ስንመለከታቸው ሁለቱም የማስጠንቀቂያ ሃሳብን ያዘሉ እንደሆኑ እናያለን፤ ቁ1-5 “ንስሃ ካልገባችሁ…” ቁ6-9 ደግሞ “ፍሬ ካላፈራችሁ…” በሚሉት ሃሳቦች ዙሪያ ያስጠነቅቃሉ። በበለሲቱ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ የወሰደበት ምክንያት፤ ተመላልሶ መጥቶ ፍሬ ሊያገኝ ባለመቻሉና፣ በለሲቱ ተተክላ ከመሬቱ የሚገኘውን ሚኒራል ከማሚጠጥ ሌላ የምታተርፈው ምንም ዓይነት ነገር ባለመኖሩ ነው።
3. ኢየሱስ በምኩራቡ ውስጥ እያስተማረ እንደነበረ ቁ10 በግልጽ ይነግረናል። ቀኑን ልዩ ያደርገዋል የምለው፤ ሁሉን የሚችለው፣ ለሰዎች የሚራራውና፣ ከእስራት የመፍታት ሃይል ያለው ኢየሱስ በዚያ መገኘቱ ልዩ ያደርገዋል እላለሁ። እኔ ከዚህ ሁኔታ መማር እንችላለን ብዬ የማምነው፤ የትም ሆንን የትም ኢየሱስ ካልመጣ በስተቀር ፈውስ እንደሌለና፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ምኩራብ መሄዷን እንዳላቋረጠች ሁሉ፤ እኛም አንድ ቀን ኢየሱስ ይመጣልኛል ብለን ወደ ቤቱ መመላለሳችንን እንዳንተው ያበረታታናል።
4. የምኩራቡን አለቃ ያስቆጣው ነገር ፈውሱ የተካሄደው በሰንበት በመሆኑ ነበረ። ከዚህ ክፍል የማያቸው ምክንያቶች ሶስት ሲሆኑ እነዚህም፤ በመጀመሪያ ደረጃ የአብርሃም ልጅ መሆኗ፣ ቀጥሎም ለረጅም ዘመናት ማለትም ለአስራ ስምንት አመታት ሁሉ ስለታሰረች፣ እስረኛነቷም በሰይጣን ስለሆነ አንድ ተጨማሪ ቀን ማደር የለባትም። የኢየሱስ ተቃዋሚዎች የእፍረት ስሜት ሲከናነቡ፤ ሌላው ህዝብ ግን በደስታ እንደተሞሉ ከቁ17 ላይ ማየት ይቻላል።
5. በዚህ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሄር መንግሥት የተመሰለባቸው ሁለት ነገሮች፤ የሰናፍጭ ቅንጣትና፣ እርሾ ናቸው። የሰናፍጭ ቅንጣትን ሲጠቀም የእግዚአብሄር መንግሥት በምድር ላይ በትንሽ ተጀምራ በማደግ እንደምትሰፋና ለብዙዎች ማረፊያና መጠለያ እንደምትሆን ሲሆን፤ እርሾን ደግሞ የተጠቀመው ትንሽ የምትመስለዋና በትንሽ የተጀመረችው የእግዚአብሄር መንግሥት ሰፊ ከሆነው አለም ጋራ በመነካካት ለውጥን እንደምታመጣ ለማስረዳት ነው።
6. ይህ ኢየሱስ የተናገረው የማስጠንቀቂያ ሃሳብ በእኛ ዘመንም ቤተ ክርስትያን በመመላለስ ብቻ፣ የክርስትናን ቋንቋ በመልመድ፣ በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ራስን ቢዚ በማድረግ፣ ከትልልቅ የእግዚአብሄር ሰዎችና ከወንጌል አገልጋዮች የቅርብ ጓደኛ በመሆን በመመላለስ ኢየሱስን ያወቁና መንግሥተ ሰማይ የመግቢያውን በር እንዳገኙ መቁጠር በዚህም ዘመን ይቻላል። በጠባቡ በር እንዲገቡ ነው ኢየሱስ የሚመክራቸው። ሰዎችን እስከወደድንና መልካምን እስካደረግን ድረስ በማናቸውም ሃይማኖት ወደ እግዚአብሄር መድረስ ይቻላል በሚለው ትምህርት ኢየሱስ ጠባብ በር ነው ያለውን ሰዎች ማስፋት መሞከራቸውን ቀጥለዋል።
7. እነዚህ ቁጥሮች ስለአብርሃም፣ ይስሃቅና ያዕቆብ የሚያረጋግጡልን አንድ እውነት ሶስቱም ሰዎች በመንግሥተ ሰማያት እንደምናገኛቸው ነው። ይህ አነጋገር የሚያሳየን ነገር፤ የእግዚአብሄርን መንግሥት የሚወርሱት ሰዎች ከአንድ አገር፣ ወይም ከአንድ ጎሳ፣ ወይም ደግሞ ከአንድ ቋንቋ ብቻ አለመሆኑንና ከሁሉም አቅጣጫ፣ ሁሉን አይነት ሰዎች ያዘለ እንደሚሆን ነው ክፍሉ ሊያስረዳን የሚሞክረው።
8. የመጣው ዜና ሊያስደነግጠውና ሥፍራውን ሊያስለቅቀው የሚችል ከባድ ዜና ነበረ፤ ሆኖም ይህ የመጣው ዜና የኢየሱስ ስሜትም ሆነ አገልግሎቱ ላይ ያስከተለው ቅንጣት የሆነ ለውጥ እንኳን አንመለከትም።

# ጥናት አሥራ ዘጠኝ ሉቃስ 14፡1-35

1. በሰንበት ቀን ይፈውስ እንደሆነ ለማየት ስህተት ፍለጋ የተነሱ ሰዎች ናቸው። ፈሪሳውያኑንና ሕግ አዋቂዎችን የጠየቀው ጥያቄ፤ በሰንበት ቀን በሽተኞችን መፈወስ ተፈቅዷል ወይስ አልተፈቀደም የሚል ነበረ። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ለጠየቃቸው ጥያቄ መልስ ከመስጠት ዝም ያሉት የራሳቸው የሆነ መልስ ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን ነገር ግን ኢየሱስ በተለያየ ጊዜ ለዚህ ጥያቄ ከላይ ባለው ምዕራፍ ጭምር በ13፡15-16 ላይ መልሱን የነገራቸው ስለሆነ ደፍረው በሰንበት መፈወስ አልተፈቀደም ማለት አልቻሉም።
2. ምንም እንኳን ተቃውሚቸው ዘወትር እየቀጠለ መሄዱን ቢያይም ኢየሱስ የሰንበት ፈውሱን የቀጠለበት ምክንያት እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ሰንበት ለሚለው ሃሳብ እነዚህ ሰዎች የተሳሳተ አመለካከት ስለነበራቸው ከእነርሱ ስህተት ጋራ ተስማምቶ መሄድ ስለማይችል፣ ሌላው ደግሞ ኢየሱስ ርህሩህ አምላክ ስለሆነ ሰው ሲሰቃይ የነበረበትን በሽታ ሌላ ተጨማሪ አንድ ቀን መሰቃየት አለበት ብሎ ስለማያምን ነው። ይህ ፈውስ ያስፈለገው ሰው የኢየሱስ ንብረቱ እንደሆነ ነው የሚጠቁመን።
3. በቁ1 ላይ ኢየሱስ በሰንበት ይፈውስ ወይም አይፈወስ እንደሆነ ለማየት በአይነ ቁራኛ ይከታተሉት እንደነበረ ስንመለከት፤ በቁ7 ላይ ደግሞ ኢየሱስ ስህተት ፈልጎ ሳይሆን በፊት ለፊቱ የሚያየው ነገር ስለነበረ የሰዎቹን ድርጊት ይመለከት እንደነበረ እናነባለን። በኢየሱስ ላይ ስህተት ይፈልጉ የነበሩት ሰዎች ምንም አይነት ስህተት ስላላገኙበት በጠየቃቸው ጥያቄዎችና መልስ ከማጣታቸው ስናይ፤ ኢየሱስ ግን ስህተታቸውን ሆነ ብሎ ሳይፈልግ እንኳን ስህተት እንዳገኘባቸው በቁ7-11 በተናገረው ንግግር ማየት እንችላለን።
4. እኔ ከተግሳጽ ይልቅ ትምህርት እንዲሆናቸው የነገራቸው ነው ብዬ የምረዳው፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ፈሪሳውያንን መገሰጽ ሲፈልግ "እናንተ ግብዞች" ወይም ደግሞ "ወዮላችሁ" እና የመሳሰሉትን ይጠቀማል፤ በዚህ ክፍል ግን ይህንን አታድርጉ፣ ይህንን አድርጉ የሚል ምክር ያዘለ ቃል ነው እኔ የማየው። ኢየሱስ ሊያስተምራቸው የፈለገው አንድና ዋነኛ እውነት በቁ11 ላይ ያጠቃለለበት ሃሳብ ነው፤ ይኸውም፡ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ዝቅ እንደሚልና፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ደግሞ ከፍ እንደሚል ነው።
5. ለተጋባዦች ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ የተናገረው ለጋበዘውም ሰው እውነትን ከመናገር ዝም እንዳላለ ከቁ12-14 ላይ ከተናገረው ንግግር እንረዳለን። የተጠሩት ሰዎች ሁሉ መልሰው ሊጋብዙት የሚችሉ አይነት ሰዎች መሆናቸውን ተመልክቶ እንደሚሆን አምናለሁ። ሁለቱ ምክሮች ተመሳሳይነታቸው፤ ሁለቱም ከፍታ የሚገኝበትን ሲጠቁሙ የመጀመሪያው ምድራዊ ከፍታ በዝቅታ እንደሚገኝ ሲያስተምር፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ ሰማያዊ በረከትና ከፍታ ዝቅተኞችን በማሰብ እንደሚገኝ መናገራቸው ተመሳሳይ ሃሳብን አያለሁ።
6. ይህ ሰው ይህንን መንፈሳዊነት የተሞላ ነገር ሲናገር ኢየሱስ በጣም ልክ እንደሆነና ይህ ትልቅ መገለጥ እንደሆነ ሁሉ በሚሰሙት መልክ እንደሚናገረው የሚጠብቅ ይመስለኛል። በእግዚአብሄር መንግሥት ማዕድ ስለመብላት ለተናገረው ሰውና፤ ለሌሎቹም በዚያ ለተሰበሰቡት ሰዎች ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት፤ የወንጌል ጥሪ ሲደርሳችሁ ምክንያት አትስጡ፤ ያለበለዚያ ግን በኍ ሁልጊዜ ተከፍቶ አይጠብቃችሁም የሚል መልዕክት ነው።
7. ኢየሱስን ለመከተል ቅድመ ሁኔታ ሆነው የተጠቀሱት ሁለት ዋና ዋና ነገሮች፤ አንደኛው ሁሉን ማለትም ራስንም ጭምር ሳይቀር መጥላት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የራስን መስቀል ተሸክሞ እሱን መከተል ናቸው። ኢየሱስ ቤተሰቦቻችንን ሁሉ እንድንጠላ ሲናገር ጥላቻን መዝራቱ ሳይሆን፤ በህይወታችን ከኢየሱስ በላይ የሚሆንና ለእርሱ ስንል ልንተወው የማንችለው ነገር መኖር እንደሌለበት የሚገልጽበት መንገድ ነው፤ ይህንንም ማለት የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ፍቅር እንደሆነና የክርስትያን ምልክቱም ፍቅር እነሆነ ስለሚናገር እርሱ ራሱ ቃሉ እንድንቃረን አያስተምረንም።
8. እነዚህን ሁለት ምሳሌዎች በመናገር ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የፈለገው እውነት፤ አንድ ሰው ኢየሱስን እከተላለሁ ብሎ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ እርሱን መከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ ቁጭ ብሎ አሥቦና አሰላስሎ ውሳኔ ላይ መድረስ እንደሚኖርበት ነው። በቁ25-27 ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ደቀ መዝሙርነት ከሚያስከፍለው ዋጋ ውስጥ ስላሉበት አስቀድሞ መተመን ያስፈልጋል።

# ጥናት ሃያ ሉቃስ 15፡1-32 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ፈሪሳውያኑንና ሰዱቃውያኑን ከጠፋው ልጅ ወንድም ጋራ የሚያመሳስላቸው ነገር እነዚያ ኢየሱስ ሃጥያተኞችን በመቀበሉ ደስተኛ ባለመሆናቸው ያጉረመረሙ ሲሆን፤ ታላቅ ወንድሙም ደግሞ በእርሱ አመለካከት ይቅርታ ሊሰጠው የማይገባው ወንድሙ ይቅርታ በማግኘቱ መቆጣቱ ያመሳስላቸዋል።
2. ጠፍቶ የነበረው በግና እንዲሁም ሳንቲሙ ጠፍተው በተገኙበት ወቅት ከባለቤቶቹ ጋራ የደስታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ የጠሯቸው ሰዎች ወዳጆቻቸውንና ጎረቤቶቻቸውን ነበረ።
3. ታናሽ ልጁ አባትየውን የጠየቀው አንድና ጥያቄ፤ የውርስ ድርሻው ተከፍሎ እንዲሰጠው ነው። የዚህ ልጅ ውሳኔ በመጨረሻው የሚጎዳው እንደሆነ አባትየው ጠንቅቆ ያውቃል፤ ሆኖም ባይሰጠ እንኳን አንድ ጊዜ የልጁ ልብ በገንዘብና በአለም ነገር የተሰረቀ በመሆኑ፤ እንዲያው ከቤተሰቡ ጋራ አለ እንዲባል ብቻ ማቆየት ስላልፈለገ ይመስለኛል። ይህ ሁኔታ ለእኛ የሚያስተምረን፤ ምንም እንኳን እግዚአብሄርም ውሳኔአችን ልቡን የሚሰብረው ቢሆን፤ እኛን ፈቃድ ተጋፍቶ ውሳኔአችንን እንደማይከለክል ይጠቁመኛል።
4. ይህ ልጅ ተመልሶ ለአባቱ ሊደረድር ያቀዳቸው ሶስቱ ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው። “አባቴ ሆይ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁ”፣ “ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም”፣ “ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቁጠረኝ” የሚሉት ናቸው። የውርስ ጥያቄ ከማምጣቱ በፊት አባቴ ብሎ ይጠራው እንደነበረ በስደት አገር ሆኖም ምንም እንኳን ከእርሱ ጋራ ያሚያገናኘውን ሰንሰለት ቆርጦ በሄደበትም ወቅት ሁሉ አባቴ ከማለት ያቆመበት ጊዜ አልነበረም። በሩቅ ሳለ(እስኪቀርብ አልጠበቀውም)፣ ራራለት፣ እየሮጠ ሄደ፣ አቀፈው፣ ሳመው የሚሉት የፍቅሩን ጥልቀት ይጠቁሙናል።
5. ልጅየው “ከእንግዲህ” የሚልውን ቃል የተጠቀመው፤ ድርሻውን አባክኖ ባዶ እጁን የሚበላው፣ የሚጠጣውና የሚለብሰው ሳይኖረው ወደ አባቱ ቤት ከተመለሰባት ቀን አንስቶ ልጅነት እንደማይገባው በራሱ ወስኗል። አባትየው ልጁ የተናገረውን ነገር ያለማድመጥ ሳይሆን፤ እኔ የሚገባኝ አባት በልጁ መምጣት ትልቅ ደስታ ውስጥ ስላለና፤ ቀድሞ ልጁ የነበረው ዛሬም ልጁ እንደሆነ ስለሚያውቅ በንግግሩ ላይ ለጊዜው ማብራሪያ በመስጠት ጊዜውን ከማጥፋት ይልቅ፤ በልጁ መምጣት ሃሴት ማድረግ ላይ ማተኮር ስለፈለገ ነው።
6. ታላቅ ወንድም በሚካሄደው ነገር ሁሉ የተሰማው ስሜት የቁጣና የሆነው ሁሉ ነገር እንዳላስደሰተው እንመለከታለን። ይህ ልጅ በቁ29 በምንመለከተው መሰረት አባቱን የሚደሰትበትንና እንደቤተሰብም የሚገባውን የራሱን ድርሻ ያደረገውን ሁሉ ልጅ ራሱን እንደ ባሪያ አድርጎ ያቀረበ እንደሆነ ስንመለከት፤ አባትየው ግን እየለፋና እየሰራ ያለው የአባቱ ንብረት ማለት የራሱ ንብረት ማለት እንደሆነ ስላልተረዳ ትምህርት እያስተማረው ነው።
7. በሶስቱም ምሳሌዎች ውስጥ የምናየቻው ሶስት ሃሳቦች፤ የመጀመሪያው ሃሳብ ከሚጠነቀቅለት ሰው ተለይቶ መጥፋት፣ ሁለተኛው በባለቤቱ አጥብቆ መፈለግና መውደድ ምክንያት መገኘት፤ የመጨረሻው ደግሞ ከደስታ ብዛት ግብዣና ደስታ ናቸው። በአጭር አነጋገር “መጥፋት”፣ “መገኘት” እና “መደሰት” ልንል እንችላለን። ከሶስቱ በብዛት የማየው ደስታን አስመልክቶ የተነገረው ሲሆን፤ ይህንንም ሃሳብ በቁ5፣ 6፣ 7፣ 9፣ 10፣ 23፣ 24፣ 25፣ 29፣ እና በቁ32 ላይ ማየት ይቻላል።
8. ሶስቱንም ምሳሌዎች በተለይም ቁ7፣ ቁ10ርንና፣ ቁ32ትን ስንመለከት የአንድ ነፍስ መዳን በሰማይ የሚፈጥረውን ልዩ ደስታ ስንመለከት፤ እኛም ነፍሳት ክርስቶስን አውቀው ደህንነት ማግኘታቸውን በታሪኩ ውስጥ እንደምናያቸው ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያንና፣ እንደ ታላቅ ወንድምየው የተለያየ ምክንያት እያነሳን ደስታችንን ሳናሰርቅ፤ የእግዚአብሄርንና የመላዕክቱን ደስታ እንድንጋራ ያስተምረናል።

<u>ጥናት ሃያ አንድ ሉቃስ 16፡1-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ሃብታሙ ሰው በመጋቢው ላይ ደስ ያልተሰኘበት ነገር፤ ንብረቱን በትክክል እንደማይጠብቅለትና እያባከነበት እንደሆነ ነው የተነገረው። በ1ኛ ቆሮ 4፡1-2 ላይ በምናነበው ክፍል ከመጋቢ ወይም ከባለ አደራ የሚጠበቀው አንድና ዋነኛ ነገር ታማኝነት ነው። መጋቢው ከሥልጣኑ ሲሻር ሊሰራቸው እንደማይፈልግና እንደማይችል አድርጎ የተናገራቸው ሁለቱ የሥራ ዓይነቶች፤ የመጀመሪያው እርሻ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ልመና ነው።
2. እርሻና ልመና እንደማያዋጡት በተረዳ ጊዜ ሊያደርግ የወሰነው ነገር አሁኑኑ በሥልጣኑ ላይ እያለና ነገሮችን ማድረግ በሚችልበት ወቅት የሰዎችን ዝምድና የማፍራት ታክቲክ ሲጠቀም ነው የምንመለከተው። ጌታ በዚህ ክፍል ውስጥ ያደነቀው ነገር መጋቢው ያደረገውን የአጭበርባሪነት ተግባር ሳይሆን፣ ማድረግ የሚችለው ነገር ባለበት ወቅት ተጠቅሞ ለወደፊቱ ድህነት ውስጥ ገብቶ ውጭ እንዳይቀር የሰዎችን ዝምድና አሁን ባለው ሥልጣኑ ተጠቅሞ ዝምድናቸውን ለመግዛት ያደረገውን ብልህ ውሳኔ ነው ያደነቀው።
3. እነዚህ ሶስቶ ኢየሱስ ትምህርት እንዲሆናቸው የተናገራቸው ነገሮች፤ የመጀመሪያው በቁ9 ላይ የምናገኘው በምድር የምናገኘውን ባለጠግነትና ሃብት ለሰማያዊው መንግሥት ሰዎችን ወይም ወዳጆችን እንድናተርፍበት፣ ሁለተኛው ቁ10-12 የሚናገረው በምድራዊ ነገር ማለትም በገንዘብ ካልታመንን በትልቁ ወይም በሰማያዊ ነገር አይሾመንም፤ ሶስተኛው ደግሞ በቁ13 ላይ የምናየው ሁለት ጌታ ሊኖረን እንደማይቻልና ገንዘብን ጌታችን ልናደርገው እንደማይገባን ያስተምረናል።
4. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናያቸው ፈሪሳውያን በሌላ ሥፍራ ከምናያቸው የሚለዩበት ነገር፤ እነዚህ ገንዘብ ወዳዶች እንደሆኑ ጸሐፊው ነግሮናል። ኢየሱስን ያስነቀፈው ነገር የትምህርቱ ትክክል አለመሆን ሳይሆን በሰዎቹ ልብ ውስጥ የነበተው የገንዘብ ወዳድነት ነው። ሰዎች በፈሪሳውያኑ ልብ ውስጥ ያለውን የገንዘብ ፍቅር ስለማይመለከቱ አክብረው ይመለከቷቸዋል፤ ነገር ግን እግዚአብሄር በልባቸው ያለውን ስለሚያውቅ ርኩስ ሆነው ያያቸዋል።
5. ከዮሐንስ በፊት ሕግና ነብያት ቦታውን ይዘው እንደነበረ፤ ከዮሐንስ በኋላ ግን የእግዚአብሄር መንግሥት እንደሆነ ይናገራል። ይህ የኢየሱስ አነጋገር አሁን ባለንበት ዘመን በክርስትያኖች ዘንድ የተሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ የምመለከተው፤ ይህንንም ማለት የቻልኩበት ምክንያት፤ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሚስትን ፈትቶ ሌላ አዲስ ሚስት ማግባት በምዕመናን ብቻ ተወስኖ ያለ ነገር ሳይሆን የቤተ ክርስትያን መሪዎችም ሳይቀሩ በዚህ ሁኔታ ውስጥ በብዛት እየገቡ እንደሆነ የአደባባይ ሚስጢር ሆኗል፤ በአለም የሚሰማው ስታትስቲክስ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ከሚገኘው ምንም እንደማይበላለጥም ሁኔታውን ያጠኑት ሰዎች ይነግሩናል።
6. አንደኛው ሃብታም፣ ያማረ ዓይነት ልብስ የሚለብስ፣ በየቀኑ በተድላ የሚኖር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ደሃ፣ በቁስል የተወረረ፣ የራሱ ቤት ያልነበረው፣ የሃብታሙን ፍርፋሪ የሚመኝና ውሾችም ቁስሉን የሚልሱት ሰው ነበረ። እነዚህን ሁለት ሰዎች እኩል ያደረጋቸው ነገር በቁ22 ላይ እንደምንመለከተው ሁለቱንም ሳይለይ እኩል ያደረጋቸው ነገር ሁለቱም መሞታቸው ነው።
7. የአብርሃም ምላሽ በመጀመሪያ ደረጃ በምድር አንተ የምትፈልገውን አይነት ኑሮ በመኖር እግዚአብሄርን ለማሰቢያና ለመፈለጊያ ጊዜ አልነበረህም፤ በተጨማሪም እኔ እንደፈለግሁ ሰውን ከወዲያ ወዲህ ማመላለስ የምችልበት ሥፍራ አይደለም። አብርሃም ሰው ሃብታም ስለሆነ ሲዖል፣ ደሃ ስለሆነ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ይገባል ማለቱ ሳይሆን፤ ለእኔ እንደሚገባኝ ሃብታሙ ሰውዬ በየእለቱ አልዓዛር በደጁ ተኝቶ ሲወጣና ሲገባ እያየው ርህራሄ ለማድረግ አለመፈለጉን እየነቀፈ ይመስለኛል።
8. አብርሃም ሲመልስ ወንድሞችህ እዚያው ህግንና ነብያትን የሚነግሯቸው ሰዎች ስላሉላቸው እነርሱን ይስሙ የሚል መልስ ነው የሰጠው። በሃብታሙ ሰው አመለካከት አምስቱ ወንድሞቹ መንግሥተ ሰማያትና ሲዖል እውነት እንደሆነ የሚያምኑት ተአምር ቢያዩ ነው የሚል እምነት ነበረው፤ ከአብርሃም አነጋገር እንደምንረዳው ግን ለሰዎች የደህንነት መንገድ ሆኖ የተዘጋጀው የእግዚአብሄርን ቃል ሰምቶ በእምነት መቀበል እንጂ ተአምራትን ማየት ብቻውን ለደህንነት እንደማያበቃ ነው።
9. አብርሃም ለዚህ ሃብታም ሰው ሊያስረዳው የፈለገው ነገር ቢኖር፤ አንድ ጊዜ ሰው ከሞተና የተመደበለትን ሥፍራ ከያዘ በኋላ ከዚህ ወደዚያ ማድረግ የሚችል ማንም እንደሌለ እንዲያው ነው።

# ጥናት ሃያ ሁለት ሉቃስ 17፡1-37 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ክፍሎች ሁሉ ስንመለከታቸው ወንድምን የመገሰጽ አላማና ግቡ ልክ መሆናችንን ለማረጋገጥ ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን ከፍቅር የመነጨና ያንን ሰው መልሶ የማቅናት፣ ወደ ትክክለኛው መንገድ ማምጣት ወይም የራሳችን ለማድረግ የሚለው ሃሳብ ነው። ሰውን አንድ ጊዜ በድሎ ተመልሶ ይቅርታ ቢጠይቅ ለብዙ ሰዎች አስቸጋሪ አይመስለኝም፤ ነገር ግን ሰው እየደጋገመ በድሎን እየተመላለሰ ደግሞ ይቅርታ ቢለን ለብዙዎቻችን አስቸጋሪ የሚሆንብን ይመስለኛል።
2. ሐዋርያቱ ኢየሱስን የጠየቁት ጥያቄ ያላቸው እምነት አነስተኛ እንደሆነ በማሰብ እምነታቸውን እንዲጨምርላቸው ነው። በእኔ አመለካከት ከኢየሱስ መልስ የምረዳው፤ እነዚህ ሰዎች አለን ብለው ያሰቡት ዓይነት ጥቂት እምነት እንኳን እንደሌላቸው፤ ወይም ደግሞ ያላቸው እምነት በትክክለኛ መንገድ በእግዚአብሄር ላይ የተመሰረተ እምነት ላይሆን እንደሚችል ይመስለኛል። እምነት ከመስማት ነው መስማት በእግዚአብሄር ቃል ነው ስለሚል፤ እምነትን ከፈለግን ትክክለኛው ምንጭ የእግዚአብሄር ቃል ነው።
3. ይህ አይነቱ አመለካከት የተሳሳተ መሆኑን የምናይበት ምክንያት፤ ጳውሎስ በቆላስይስ ለሚኖሩት ጌቶች የተናገረው፤ በመጀመሪያ ደረጃ እነርሱም ራሳቸው በሰማይ ጌታ እንዳላቸው፤ ስለዚህም አገልጋዮቻቸውን ፍትህ በተሞላበትና ቅንነት ባለው መንገድ ማስተዳደር እንደሚያስፈልጋቸው ስለሚናገር ኢየሱስ ይህንን መቃወሙ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን ሊያስተላልፍ የፈለገው ሃሳብ እንዳለ እናያለን። ጌታን ስናገለግል ምስጋናን ጠብቀን ሳይሆን፤ ትህትና በተሞላ ልብ ከቁጥር የማንገባ እንደሆንን በመገንዘብ ማድረግ የሚገባንን ብቻ እንዳደረግን በመቁጠር ማገልገል እንደሚኖርብን ያስገነዝበናል።
4. እነርሱ በርቀት ቆመው ነበረ፤ እርሱ ግን በቅርብ በመሆን እግሩን ነክቶ ነው፤ የእነርሱ ልመና በታላቅ ድምጽ ነበረ፤ የእርሱ ደግሞ ምስጋናው በታላቅ ድምጽ፤ አንደበታቸው ጌታ ሆይ ይለው ነበረ፤ እርሱ ግን ወድቆ ለጌትነቱ ይሰግድ ነበረ። በቁ19 ላይ የምናነበው ይህ የኢየሱስ አነጋገር የሚጠቁመን ነገር፤ በቁ16 ላይ በኢየሱስ እግር ላይ በፊቱ ተደፍቶ እንደሚለው፤ እንዲያው ደፋ ብሎ ቀና ያለ ሳይሆን፤ ኢየሱስ ተነሳ እስካለው ጊዜ ድረስ በኢየሱስ እግር ላይ በፊቱ ተደፍቶ መቆየቱን ነው የሚያሳየን።
5. እንዲያውቁት የፈለጋቸው ሶስት ነገሮች 1) የእግዚአብሄር መንግሥት በሚታዩ ምልክቶች እንደማትመጣ ማለትም በዓይን የሚታይ ነገር እንዳልሆነ 2) ሰዎች እዚህ ወይም እዚያ ነው ማለት የሚችሉት አይደለችም ማለትም በቦታ የምትወሰን አይደለችም 3) የመጨረሻው እውነት ደግሞ የእግዚአብሄር መንግሥት በመካከላቸው እንዳለች፤ ማለትም የእግዚአብሄር መንግሥት ወኪል የሆነው ኢየሱስ በመካከላቸው መኖሩ ነው።
6. ኢየሱስ ይህንን ሲል ሊነግራቸው የፈለገው ነገር፤ የሰው ልጅ ሲገለጥ የተሰወረና ሰዎች ይኸው እዚህ መጥቷል ይባላል፤ ወይም እዚያ ተገልጧል ተብሏል የሚሉት ዓይነት ሳይሆን ማንም ሰው ሊስተው በማይችለው አይነት እንደሚመጣ ለማስረዳት ነው።
7. ከጌታ መምጣት ጋራ በማነጻጸር የተነገሩት ሁለት ዘመኖች፤ የኖህና የሎጥ ዘመን ተብለው ነው የተጠቀሱት። በነዚህ በሁለት ዘመኖች ውስጥ ይካሄዱ የነበሩት ነገሮች፤ ሰዎች ይበሉና ይጠጡ ነበር፣ ሰዎች ያገቡና ይጋቡ ነበር፣ ሰዎች ይገዙና ይሸጡ ነበረ፣ ተክል ይተክሉና ቤት ይሰሩ ነበረ።
8. ኢየሱስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረውን ሃሳብ በሁለት ወይም በሶስት ቃላት መግለጽ ቢያስፈልግ በእኔ አመለካከት፤ “ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ” ወይም ደግሞ “ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ” ማለት እችላለሁ።

## ጥናት ሃያ ሶስት ሉቃስ 18፡1-42 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ለመበለቲቱ ፍርድ ለመስጠት ያልፈለገው ሰው፤ በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሄርን የማይፈራ ሰው እንደነበረ ተነግሮናል፤ በተጨማሪም ደግሞ ይህ ሰው ሰውንም በጭራሽ የማያከብር እንደሆነም እናነባለን፤ ሰውየው የሚኖረው መበለቲቱ በምትኖርበት ከተማ ውስጥ እንደነበረም እናውቃለን፤ ፍርድን መስጠትም መከልከልም እንደሚችልም ይታያል። ሴቲቱ መበለት በመሆኗ ከጎኗ ቆሞ ሊረዳት የሚችል ባል አለመኖሩና፤ ምናልባትም ደግሞ ገንዘብ ኖሯት መከራከር የማትችልበት ሁኔታ ላይ መሆኗ ሊያስጠቃት እንደሚችል ጥርጥር የለውም።
2. የትምህርቱ ትኩረት ገና ቁ1 ላይ ሲጀምር እንደተናገረው በአብዛኛው በመበለቲቱ ላይ እንድናተኩር እንደፈለገ ነው የምረዳው፤ አስቀድሞም ምሳሌው የተነገረው ሳንታክት ሁልጊዜ እንድንጸልይ በመሆኑ፤ በዳኛው ድርጊቶች ላይ ሳይሆን በመበለቲቱ አለመታከት ላይ ያተኩራል። እግዚአብሄር ለመበለቶች ይራራል፣ እግዚአብሄር ጭቅጭቅ ስለሚበዛበት አይፈርድም፣ እግዚአብሄር ለሰው ልጆች አክብሮት አለው።
3. ራሱን ከፍ የሚያደርግ ዝቅ እንደሚልና፤ ራሱን የሚያዋርድ ደግሞ ከፍ እንደሚል በመናገር ነው ያጠናቀቀው። ይህ የኢየሱስ አነጋገር ከላይ ታሪካቸው የተነገረላቸውን ሰዎች የሚነካበት መንገድ፤ ፈሪሳዊው ጸሎቱንም ሆነ ምስጋናውን የጨረሰው በመጀመሪያ ደረጃ ሌሎችን በመናቅ፤ ራሱን ደግሞ ከፍ በማድረግ ሲሆን፤ ቀራጩ ግን የርሱን አለመብቃትና የእግዚአብሄርን ቅድስና በማየት በትህትና የቀረበ መሆኑን ከፍሉ ያስረዳናል።
4. እነዚህን ሁለት ምሳሌዎች የሚያመሳስላቸው ነገር ሁለቱም ትኩረት ያደረጉበት ነገር ጸሎት መሆኑ ሲሆን፤ እነዚህኑ ምሳሌዎች የተለያዩ የሚያደርጋቸው ነገር ደግሞ የተነገሩበት ምክንያት ሲሆን፤ ከቁ1-8 ላይ ያለው ሳይታክቱ መጸለይን ለማስተማር የተነገረ ሲሆን፤ በ9-14 ላይ የተነገረው ደግሞ ከትዕቢት ይልቅ ትህትና በእግዚአብሄር ፊት እንደሚያስከብር ለማስተማር የተነገረ ነው። በቁ9 ላይ የተጠቀሱት ሰውን እንደ ትዕቢተኛ የሚያስቆጥሩት ሁለት ነገሮች "ራስን ጻድቅ አድርጎ በመቁጠር መመካትና" "ሌሎችን በንቀት ዓይን መመልከት" ናቸው።
5. ደቀ መዛሙርቱ የልጆች ወደ ኢየሱስ መምጣት ኢየሱስን ሥራ የሚያስፈታና አስፈላጊ ያልሆነ ነገር አድርገው የሚያዩት ነገር ሲሆን፤ ለኢየሱስ ግን የልጆቹ ወደ እርሱ መምጣት መከልከል እንደሌለባቸው፤ እንዲያውም የእግዚአብሄርን መንግሥት ነገር ለማስተማር ጥሩ ምሳሌዎች አድርጎ ነው ያየው። ልጆች የተነገራቸውን ነገር በእምነት ያለምንም ጥርጣሬ እንደሚቀበሉ ሁሉ፤ የእግዚአብሄርንም መንግሥት ሰዎች በሙሉ እምነት ጥርጣሬ ሳይኖርባቸው መቀበልን የሚጠቁመን ሃሳብ ነው።
6. ይህ ሰው እንዲያደርግ የተጠየቀው አንድ ነገር ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆች እንዲሰጥና ያንን ካደረገ በኋላ ኢየሱስን እንዲከተል ነበረ። ለዚህ ሰው ኢየሱስን ለመከተል እንቅፋት ሆኖበት የምናየው ነገር ባለጠግነቱ ወይም ገንዘብ እንደሆነ ነው። ኢየሱስ ነገሮችን ማከበድና እንዳይከተሉት የማባረር ሃሳብ ሳይሆን፤ ሰዎች የሚገቡበትን ነገር በመረዳትና ገብቷቸው እንዲገቡበት እንጂ እንደ እኛ የሚከተሉትን ሰዎች ቁጥር ለመጨመር ያህል ብቻ እውነቱን አይሸፋፍንም።
7. ሰዎች በኢየሱስ ላይ የሚያደርጓቸው፡ ለአህዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፣ አህዛብ ያፌዙበታል፣ ያንገላቱታል፣ ይተፉበታል፣ ይገርፉታል፣ በመጨረሻም ይገድሉታል። ኢየሱስ የሚያደርገው አንድ ነገር ደግሞ፡ በሶስተኛው ቀን ከሙታን ይነሳል።
8. ይህ እወር ሰው እስከዛሬ በዚያ ሥፍራ ሲለምን የቆየው ከአላፊ አግዳሚው ሳንቲሞችን ለመቀበል ነበረ። ይህ ሰው ከኢየሱስ ጋራ መገናኘቱና ፈውሱን መቀበሉ የነበረበትን ሥፍራ ትቶ ኢየሱስን የሚከተል፤ ምለትም ህይወቱን ከኢየሱስ ጋራ ያስተሳሰረ ሰው እንደሆነ፤ በተጨማሪም ደግሞ ህይወቱ የምሥጋና ህይወት እንደተሞላም እናነባለን።

<u>ጥናት ሃያ አራት ሉቃስ 19፡1-48 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ዘኪዎስ በኢያሪኮ ከተማ የሚኖር ሰው ነበረ፣ ዋና ቀረጥ ሰብሳቢ ነበረ፣ ሃብታም ሰው ነበረ፣ ኢየሱስን የማየት ፍላጎት የነበረው ሰው ነበረ፣ ቁመቱ አጭር ነበረ። በእኔ አመለካከት ይህ ሰው ህጻን አይደለም፣ ምናልባትም በእድሜውም ገፋ ሳይል አይቀርም፣ ከዚያም በላይ በአካባቢው ሃብታም ሰው መሆኑም ዛፍ ላይ ከምወጣ ኢየሱስን ማየቱ ይቅርብኝ ሊያሰኘው እንደሚችል አስባለሁ።
2. በ18፡22-23 ላይ የምናየው ሃብታም ኢየሱስን የመከተል ፍላጎት ቢያሳይም እንኳን ያለውን ነገር ለመጣል ፈቃደኛ አለመሆኑን ይህም ለኢየሱስና ለሃብቱ እኩል ቦታ መስጠቱ ሃዘን እንዳመጣበት ቁ23 ሲያሳየን፤ ዘኬዎስ ደግሞ ኢየሱስን ማግኘቱ በህይወቱ ያመጣውን ደስታ ቁ6 የሚነግረን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ሳይጠይቀው ያለውን ለመስጠትም ፈቃደኛነቱን ሲገልጥ እናነባለን። አብርሃም የእምነት አባት በመሆን የሚታወቅ ስለሆነና ዘኪዎስም ኢየሱስን በእምነት ስለተቀበለው ገላ 3፡7 በሚናገረው መሰረት ነው።
3. ቁ13 እንደሚነግረን አስሩን አገልጋዮቹን እንደጠራና እንደሰጣቸው ነው የምናነበው። ከነዚህ እንዲነግዱ ከተሰጣቸው አሥር ሰዎች መሃል እንዳተረፉና እንዳላተረፉ ሲጠየቁ የምንመለከተው ሶስቱ ብቻ ናቸው። ለአስሩ እንዲነግዱ ሰጥቶ ሲመለስ ሶስቱን ብቻ እንደጠየቀ የምናይበት ምክንያት፤ ለእኔ እንደሚገባኝ ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ሊያስተምር ያሰበው ሃሳብ በእነዚህ ሶስት ሰዎች ጥያቄና መልስ የተካተተ ስለሚሆን በተጨማሪ ሃተታ ምሳሌው እንዳይንዛዛ በማለት እንጂ ሌሎቹ አልተጠየቁም ለማለት አይመስለኝም።
4. ይህ ሁሉ የተነገረለት ኢየሱስ ነው እላለሁ፤ ይህንንም ማለት ያስቻለኝ ኢየሱስ ለአገልጋዮቹ ስጦታን እንደሚሰጥ፣ የንጉስነት ማዕረጉን ተቀብሎ ወደምድር ዳግም እንደሚመጣ፣ ስጦታን የሰጣቸው አገልጋዮቹ በተሰጣቸው ስጦታ ሰርተውበት ወይም አልሰሩበት እንደሆነ እንደሚጠይቅና እንደሚቆጣጠር የተጻፈ ነገር በመሆኑ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ወደ ኢየሱስ የሚጠቁሙ ናቸው ብዬ አምናለሁ። ይህ አገልጋይ ጌታው በሰጠው ገንዘብ ሰርቶ እንዳያተርፍ የከለከለው ነገር "ፍርሃት" ይባላል።
5. የእነርሱ ተቃውሞ ያኛው ባሪያ አሥር ምናን ስላለው ተገቢ ሆኖ አላዩትም። "እላችኋለሁ ላለው ሁሉ ይጨመርለታል፤ የሌለው ግን ያው ያለው እንኳን ይወሰድበታል።" ማለት፤ እነዚያ ያተረፉት አገልጋዮች በተሰጣቸው ነገር እንደሚገባ የሰሩና የደከሙ በመሆኑ ብዙ እንዲኖራቸው ሆነዋል፤ አንደኛው አገልጋይ ግን እኩል የተሰጠውም እንኳን ቢሆን ባለመስራቱና ባለመድከሙ ማትረፍ አልቻለም፤ ስለዚህም ኢየሱስ ያለው ማለቱ ሰርቶ ያተረፈው ለማለት እንጂ ለመኖር ለመኖርማ ሁሉም እኩል ነበረ ያላቸው፤ ስለዚህ ከሌለው ይወሰድበታል ማለት ስላልሰራና ስላላተረፈ ያለውም ጭምር ይወሰድበታል ማለቱ ነው።
6. መልዕክተኞቹ የተነገራቸው ነገር፡ በፊታቸው ባለችው መንደር ሲገቡ ማንም ሰው ያልተቀመጠበት ውርንጫ ታስሮ እንደሚያገኙና ፈትተው እንደሚያመጡ፤ ለምን እንደሚፈቱ ሲጠየቁ ደግሞ ለጌታ እንደሚያስፈልገው እንዲናገሩ ነበረ። ከሆኑት ሁኔታዎች መሃል ሶስት ነገሮች ያስገርሙኛል፡ በመጀመሪያ ደረጃ ውርንጫዋ በተባለችበት ሥፍራ መገኘቷ፣ ውርንጫዋ ሰው ተቀምጦባት አለማወቁና፤ "ለጌታ ያስፈልገዋል" ሲባሉ ባለቤቶቹ ዝም ብለው መልቀቃቸው አስደናቂ ይሆንብኛል።
7. ለኢየሱስ እነዚህ ሰዎች አምልኳቸውን እየሰጡ ያሉት በደብረዘይት ተራራ ቁልቁል በሚወስደው መንገድ ላይ፤ ማለትም በቤት ውስጥ ሳይሆን በውጭ ነበረ። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለይም ቁ39 ላይ የምናያቸው ፈሪሳውያን በዙሪያቸው እየተካሄደ ላለው ነገር ጭራሽ አይኖቻቸው የታወሩባቸውና እየሰሙም እንደማይሰሙ ጆሮዎቻቸው የተደፈኑ ስለሆኑ ኢየሩሳሌምን ይወክላሉ እላለሁ።
8. ኢየሱስ በቁ45-48 ውስጥ በምናየው ምንባብ፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ገብቶ የሚያደርጋቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ሻጮችና ለዋጮችን ማስወጣት ሲሆን፣ ሁለተኛው ነገር ደግሞ ቤተ መቅደሱን ከወንበዴዎች ካጠራ በኋላ ቁ47 እንደሚነግረን፤ በየቀኑ ለንግድ ሳይሆን ለመማር የመጡትን ያስተምር እንደነበረ እናነባለን።

# ጥናት ሃያ አምስት ሉቃስ 20፡1-47 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሊገድሉት እየፈለጉ ያሉት ሰዎች፡ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና የህዝብ ሽማግሌዎች ሲሆኑ፤ ኢየሱስንም የጠየቁት ሁለት ጥያቄዎች፤ የመጀመሪያው "እነዚህን ነገሮች የምታደርገው በምን ሥልጣን እንደሆነ ንገረን" የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "ሥልጣንስ የሰጠህ ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?" የሚሉ ናቸው።
2. በነዚህ ሰዎች አመለካከት አንድን ነገር ሰው በእርግጠኛነት ለመቀበልና ለማመን ካስፈለገ ምንጬ ሰማያዊ መሆን እንዳለበት ነው የተስማሙት። እነዚህ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና፣ ሽማግሌዎች "ከሰማይ ወይስ ከሰው" የሚለውን ሃሳባቸውን ስንረዳ ለማለት የፈለጉትና ሰማይ በሚለው ቃል ቦታ ልንተካ የምንችለው ቃል "እግዚአብሄር" የሚለውን ነው፤ ጥያቄአቸውን እንደገና ብናሰፍረው "የዮሐንስ ጥምቀት ከእግዚአብሄር ነበር ወይስ ከሰው?" ለማለት ፈልገው ነው።
3. በዚህ ምሳሌ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የእርሻው ባለቤት የላካቸውን መልዕክተኞቹን የደበደቡ፣ ያቆሰሉና ያዋረዱ፣ በመጨረሻም ደግሞ ልጁን የገደሉት መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታዎች ላይ አይሁዶች የእግዚአብሄርን ነብያትና መልዕክተኞች እንደገደሉ የተናገረ ሲሆን፤ በመጨረሻም እንደምናውቀው ወራሽ የሆነውን ኢየሱስን ገድለውታል። የእርሻው ባለቤት የወይኑን ተክል ቦታ ከገበሬዎቹ ወስዶ ለሌሎች ሰራተኞች ወይም ገበሬዎች ይሰጣል ይላል።
4. ከላይ የእርሻው ባለቤት የላካቸውን መልዕክተኞች የደበደቡትና ያሰቃዩት፤ እንዲሁም ልጁን የገደሉት አህዛብ ናቸው ካልን፤ በዚህ ሥፍራ "ሌሎች" በመባል የተነገረላቸው የወንጌል የመዝራት ሃላፊነት ከአይሁድ ተወስዶ የተሰጠው ለአህዛብ በመሆኑ የሚናገረው ስለ አህዛብ ነው እላለሁ። ጸሐፍትና የካህናት አለቆች ኢየሱስ የተናገረውን ነገር ሰምተው በንስሃ ወደ እግዚአብሄር ከመመለስ ይልቅ ሊይዙትና ሊገድሉት እንደፈለጉ እናነባለን።
5. ኢየሱስን ለማጥመድ የተላኩትን ሰዎች በተለይም ቁ20 የሚገልጻቸው "ጻድቃን መስለው የሚቀርቡ ሰላዮች" ይላቸዋል። እነዚህ አስመሳዮች ፈተናቸውን ከመፈተናቸው በፊት ስለ ኢየሱስ በቁ21 ላይ የተናገሯቸው ነገሮች፡ አንተ ትክክለኛውን ነገር ትናገራለህ ትክክለኛውንም ነገር ታስተምራለህ፣ የእግዚአብሄርን መንገድ በእውነት ታስተምራለህ፣ ለማንም ደግሞ አታደላም የሚሉት ናቸው። በአሁኑ ዘመን ያሉትም የጌታ አገልጋዮች በአንደበታቸው የሚናገሩት ነገር ከወንጌል ሃሳብ ውጭ የሆነ፣ ጥበብ የሌለውን ንግግር በመናገር ለእግዚአብሄር ሥም መሰደቢያ፣ ለራሳቸውም የመውደቂያ ምክንያት እንዳይሆኑ ሊጠነቀቁ ይገባል።
6. ይህ ኢየሱስ ያለፈበት ሁኔታና የሰጠው ምላሽ ለአማኞች የተሰጠውን መመሪያ የሚያሟላው፤ በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ኢየሱስ ለሚሰነዘርበት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሙሉ ለሙሉ ዝግጁና አጥጋቢ፣ ጥበብ የተሞላባቸውን መልሶች መመለስ እንደቻለ እንመለከታለን። ኢየሱስን መግደል በሚለው ሃሳብ ፈሪሳውያን፣ ጸሐፍትና፣ እንዲሁም ሰዱቃውያን ሁላቸው ይስማሙ እንጂ፤ ሐዋ ሥራ 23፡8 እንደሚነግረን ትንሳኤን አስመልክቶ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ከሰዱቃውያን ፍጹም የተለየ አመለካከት ስለነበራቸው፤ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ትንሳኤ እንዳለ በመናገሩ የተነሳ ነው ጸሐፍቱ መልካም እንደተናገረ የነገሩት።
7. ጸሐፍት የሚባሉት፤ ዘርፋፋ ቀሚስ ለብሰው መዞር ይወዳሉ፣ በገበያ ቦታ ሰላምታ፣ በምኩራብ የከበሬታ መቀመጫ፣ በግብዣ ቦታ የክብር ሥፍራ ይፈልጋሉ፣ የመበለቶችን ቤት ያራቁታሉ፣ ለታይታ ጸሎታቸውን ያስረዝማሉ። ስለጻህፍት ኢየሱስ የተናገረውን ተግሳጽ እንዲሰሙት የፈለገው ከደቀ መዛሙርቱ አልፎ ሕዝቡ ይሰሙት እንደነበረ ከቁ45 ላይ መረዳት ይቻላል።
8. በቁ27-33 ውስጥ የምንመለከታቸው ሰዱቃውያን የእግዚአብሄርን ቃል ሲጠቀሙበት የምናየው፤ ኢየሱስን በሚናገረው ቃል ለመያዝና ለማጥመድ ሲሆን፣ ይህንንም በማድረግ እነርሱ ትንሳኤ የለም የሚል እምነት ስለነበራቸው፤ ለጠየቁት ጥያቄ ኢየሱስ የሚሰጠው መልስ ወሳኝነት ያለው ብቻ ሳይሆን፤ ይህ የያዙት እምነት ትክክለኛ መሆኑንም ለሰው ሁሉ የሚያረጋግጡበት መንገድ ነበረ።

## ጥናት ሃያ ስድስት ሉቃስ 21፡1-38 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቤተ መቀደሱ ውስጥ የምናያቸው ሰዎች ሶስት ዓይነት ሰዎች ሲሆኑ፤ እነዚህም፡ ሃብታሞች፣ ድሃ መበለትና ኢየሱስ ናቸው። ሃብታሞቹ ሰዎችና ድሃዋ መበለት ሁላቸውም መባቸውን በመባ መሰብሰቢያው ውስጥ ይጨምሩ ነበረ፤ ኢየሱስ ደግሞ እዚያ ቆሞ በመባ ውስጥ የሚጥሉትን ሰዎች ይመለከት ነበረ። ኢየሱስ ስጦታቸውን ያወዳደረበት መለኪያው ምን ያህል እንደሰጡ ሳይሆን ምን ያህል እንዳላቸውና ካላቸው ውስጥ ደግሞ ምን ያህሉን እንደሰጡ ነው።
2. ከቁ1-4 ባለው ክፍል ላይ ትምህርቱን የመሰረተው በተመለከተው ነገር ላይ ሲሆን፤ ከቁ5 ጀምሮ ላለው ትምህርቱ መነሻ አድርጎ የተጠቀመው ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ሲነጋገሩ የሰማው ነገር ነው። በደቀ መዛሙርቱ አዕምሮ ውስጥ የተፈጠሩትና ጌታን የጠየቁት ሁለት ጥያቄዎች፤ ይህ ሁሉ የሚሆነው ወይም ቤተ መቅደሱ የሚፈርሰው መቼ ነው? ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ፤ ይህ ሁሉ እንደሚሆን ምልክቱ ምንድነው የሚሉ ናቸው።
3. አንደኛው ቁ8 ላይ የምናየው "እንዳትስቱ ተጠንቀቁ" የሚለው ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ "እናንተ ግን እነርሱን አትከተሏቸው" የሚል ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ ቁ9 ላይ የምናገኘው "አትደንግጡ" የሚል ነው። በኢየሱስ ስም የሚመጡት ሰዎች በመጀመሪያ ደረጃ የሚሉት ነገር "እኔ ኢየሱስ ነኝ" በማለት ለማሳመን መሞከር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "ጊዜው ቀርቧል" ነው የሚሉት። እነዚህን ስንሰማ መደንገጥ የማይኖርብን መጨረሻው ከመምጣቱ በፊት እነዚህ ነገሮች አስቀድመው መሆን ያለባቸው ነገሮች ስለሆኑ ነው።
4. ከላይ ከቁ9 ጀምሮ የተዘረዘሩትን ነገሮች ማለቱ ነው። ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ መነሳት፣ ታላቅ የመሬት መናወጥ፣ በተለያየ ሥፍራ ረሃብና ቸነፈር፣ ከሰማይ ታላቅ ምልክት ይሆናል። በክርስቶስ ተከታዮች ላይ እንደሚደርስ የተነገሩት ነገሮች ከዘመናት ጀምሮ ክርስትያኖች ሲያልፉበት የነበረ ነገር እንደሆነ የታወቀ ነው፤ ሆኖም በዚህ ሥፍራ የሚናገረው ግን በአንድ ሥፍራ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በየአገራቱና በየአህጉራቱ የሚደረግ በስፋቱና በመጠኑ ከሌሎቹ የተለየ እንደሚሆን ነው የማምነው።
5. አማኞች በሌላ በምንም መንገድ ማግኘት የማይችሉትና በቁ12 ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ሲደርሱባቸው ብቻ የሚከፈተው እድል፤ ቁ13 ላይ ኢየሱስ የሚነግረን ስለ ጌታ የመመስከር ጥሩ እድል ይገጥማችኋል ነው የሚለን። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ራሳችንን ስናገኘው እንዳንጨነቅ የነገረን ምክንያት፤ ተቃዋሚዎቻችን ሊቋቋሙት የማይችሉትን ቃል ብቻ ሳይሆን ጥበብንም በዚያ ሰዓት ስለሚሰጠን ነው።
6. በዚህ ስፍራ የተጠቀሱት ሰዎች ሁሉ በደህናው ሰዓት ለእኛ የሚቆሙ፣ የሚወዱንና የሚጠነቀቁልን ሰዎች ናቸው። አንዳንዶቻችንን ሊገድሉን እንኳን እንደሚችሉ የተነገረላቸው እነዚህ ይከላከሉልናል፣ ይወዱናልና፣ ይጠነቀቁልናል ያልናቸው መሆናቸው ይከብደኛል፤ በሰዎች ሁሉ ዘንድ የተጠሉ መሆንም ከባድ ስለሆነ እኔ የትኛውን እንኳን እንደምመርጥ አላውቅም፤ ሆኖም ይህንን ሁሉ ጌታችን አስቀድሞ መናገሩ ልባችንን ያዘጋጃል ብዬ አምናለሁ። የተስፋ ቃሉ "ከራሳችሁ ጸጉር አንዷ እንኳን አትጠፋም" የሚል ነው።
7. "የተጻፈው ነገር ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይህ የበቀል ጊዜ ነውና፤ በምድሪቱ ላይ ታላቅ መከራ ይሆናል፤ በዚህ ህዝብ ላይ ቁጣ ይመጣል" በማለት በኢየሩሳሌምና በህዝቧ ላይ በተለያዩ ነብያቱ የተናገረውን ይፈጽመዋል (ሆሴ 9፡7)። በአለም ያሉት ሰዎች በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚሰማቸው የፍርሃት፣ የድንጋጤና፣ የመታወክ መንፈስ ነው። አማኞች ግን እነዚህ ሁኔታዎች መፈጸም ሲጀምሩ መዳናቸው ስለቀረበ ቀጥ ብለው እንዲቆሙና ራሳቸውን ወደላይ ቀና እንዲያደርጉ ነው የተነገራቸው።
8. በዚህ ቁጥር ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ቁ34 ላይ የምናየው፤ ገደብ በሌለው ህይወት፣ በመጠጥ ብዛትና ስለኑሮ በመጨነቅ ልባቸው እንዳይዝልና ያ ቀን እንደወጥመድ ድንገት እንዳይደርስባቸው እንዲጠነቀቁ ሲሆን፤ በአንጻሩ የሰጣቸው ምክር ደግሞ በቁ36 ላይ የምናየው፤ ከመመጣው ነገር ሁሉ አምልጠው በሰው ልጅ ፊት መቆም እንዲችሉ ካስፈለገ፤ ሁልጊዜ ተግተው መጸለይ እንደሚኖርባቸው ነው የተመከሩት።

## ጥናት ሃያ ሰባት ሉቃስ 22፡1-71 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን የት አግኝተውና በምን ሁኔታ ማስወገድ እንደሚችሉ እርስ በእርሳቸው የሚወያዩበት ጊዜ ነበረ። ይህ በዚህ እንዳለ፤ የአስቆሮቱ ይሁዳ ደግሞ ሰይጣን ገብቶበት ኢየሱስን እንዴት አሳልፎ እንደሚሰጠው በማሰብ ወደነዚህ ለዚህ ሃሳብ ራሳቸውን ወደ ሰጡት ሰዎች በመሄድ ኢየሱስን የሚፈልጉ ከሆነ እርሱ እንደሚረዳቸው ነገር ግን ገንዘብ መስጠት እንደሚኖርባቸው በመንገር ያስማማቸዋል። ሰዎቹ ይህ አጋጣሚ በእጃቸው ሲገባ እግዚአብሄር ራሱ ይህንን ሰው አሳልፎ ሰጠን የሚሉ ይመስለኛል።
2. ይህንን የኢየሱስ መመሪያ ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ምንም በማያሻማ ሁኔታ እያንዳንዱን ደረጃ በደረጃ ሊሆን ያለውን ነገር ሁሉ ለመልዕክተኞቹ ለመናገር መቻሉ ተልዕኳቸውን ልዩ ያደርገዋል። ጴጥሮስና ዮሐንስም ደግሞ ጌታቸው የተናገራቸውን ቃል ሙሉ በሙሉ ተቀብለው በመሄድ ሁኔታው ሁሉ ኢየሱስ እንደተናገረው ሆኖ እንዳገኙት ቁ13 ይነግረናል።
3. ለነዚህ ደቀ መዛሙርት በዚህ ቦታ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ የተገኘው ነገር፤ ከመካከላቸው ማን እንደሚበልጥ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። ኢየሱስ በቁ26 ላይ የራሱን ተከታዮች እያወዳደረ የምናየው ከአህዛብ ገዥዎች ጋራ ሲሆን፤ የእርሱ ተከታዮች የተለዩ መሆን እንደሚኖርባቸው ነው የሚያስገነዝባቸው። ከራሱ ህይወት እንዲቀስሙ የፈለገው ትምህርት፤ እኔ ከእናንተ የበላይ ሆኜ ሳለሁ እናንተ በማዕድ ተቀምጣችሁ እኔ የማገለግላችሁ ከሆነ፣ ከእናንተም መሃል ትልቁ ማን እንደሆነ ማወቅ ከፈለጋችሁ ሌላውን የሚያገለግለው እንጂ ተገልጋዩ አይደለም የሚል ትምህርት ነው ያስተማራቸው።
4. ጴጥሮስም ሆነ አብረውት የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ የማያውቁት ኢየሱስ የነገራቸው እውነት፤ ጠላታቸው ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራቸው እንደለመነና ኢየሱስ ደግሞ በተለይም ለጴጥሮስ እንደጸለየ እናያለን። ጠላታችን ሰይጣን ምንም እንኳን እኛን የማጥቃትና ዘወትር ውድቀታችንን የሚመኝ እንደሆነ ቢታወቅም፤ በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው ማድረግ ያሰበውን ለማድረግ ያለ እግዚአብሄርን ፈቃድ ምንም ሊያደርግ እንደማይችልና መለመን እንደነበረበት እናያለን።
5. ኢየሱስ “ይበቃል” ብሎ ሲናገር፤ ሁለት ሰይፍ ከያዝን ሌላ መጨመር አያስፈልገንም በዚሁ ማሸነፍ እንችላለን ለማለት አይመስለኝም፤ ነገር ግን በዚህ ዓይነት የሥጋዊ አመለካከት መመላለስ ይበቃል እንዳለ ነው የሚገባኝ። በነዚህ ሁለት ክፍሎች ውስጥ የሚታየው ነገር ጴጥሮስ በእርግጠኛነትና ከልቡ የሆነ ቃል ኪዳን ለኢየሱስ ገብቶ፤ ብዙም ሳይቆይ የገባውን ቃል ኪዳን ሰብሮ ጌታውን ሲክድ ነው የምንመለከተው።
6. አንዳንድ ጊዜ እኛ አቅማችንን አናውቅም፤ ስለዚህም ጴጥሮስ ሲዋሽ ሳይሆን እውነትም ማድረግ የሚችል የመሰለውን ነገር ነበረ የተናገረው፤ ኢየሱስ ግን አቅማችንን ያውቃል! የሰው ልጅ ተአምር ስለተደረገና ታላላቅ ተአምራቶችን ከእግዚአብሄር ስላላየ ሳይሆን የማያምነው ከእግዚአብሄር መንፈስ ውጭ የልባችን ጥንካሬና እንቢተናነታችን ስላለ በተአምራት የምንሸነፍ ሰዎች እንዳልሆንን ይህ ክፍል ያረጋግጥልናል።
7. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሥጋ መሳሪያ ማለትም በስጋዊ ሰይፍ የሰው ጆሮ ያቆሰለው ጴጥሮስ፤ በሐዋ ሥራ 2 ውስጥ ስናየው ግን የሥጋን ሰይፍ መጠቀም አቁሞ በመንፈስ ሰይፍ የሶስቱን ሺህ ሰዎች ልብ እንደማረከ እናያለን። በቁ63-65 ላይ የምናያቸው ባቂዎች የጠየቁት ነብይነቱን እንዲያረጋግጥላቸው ሲሆን፤ የካህናት አለቆቹና ሽማግሌዎቹ ደግሞ ኢየሱስ እንዲነግራቸውና ከአፉ ለመስማት የፈለጉት ነገር፤ እርሱ የእግዚአብሄር ልጅ መሆን አለመሆኑን ነበረ።
8. ኢየሱስ የደረሰበት ሐዘንና የልብ ጭንቀቱ ወደ አባቱና አምላኩ ያቀረበው እንደሆነ ስንመለከት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም የእርሱን ያህል አይሁን እንጂ እንደ አቅማቸው መጠን ሐዘን እንደነበረባቸው እናያለን። ደቀ መዛሙርቱ የተሰማቸውን ሐዘንና ጭንቀት ማስወገድ የሞከሩበት መንገድ ደግሞ እንቅልፍ እንደነበረ እናነባለን።

# ጥናት ሃያ ስምንት ሉቃስ 23፡1-56 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ኢየሱስ በዚህ ክፍል የተከሰሰባቸው ሶስቱ ክሶች፡ ሕዝባችንን ያስታል፣ ለቄሳር ግብር እንዳይከፈል ይከለክላል፣ እኔ ክርስቶስ ንጉስ ነኝ ይላል የሚሉ ሲሆኑ፤ ከነዚህ ከሶስቱ ክሶች መሃል አንድም እውነት እንደሌለ ደግሞ ግልጽ የሆነ ነገር ነው። ከሶስቱ ክሶች መሃል ጲላጦስ ትኩረት ሰጥቶ ከኢየሱስ መልስ ለማግኘት የሞከረው፤ እርሱ የአይሁድ ንጉስ መሆን አለመሆኑን ነበረ።
2. ሄሮድስ ኢየሱስን ማየት ይፈልግ የነበረበት ዋነኛ ምክንያት ቁ8-9 እንደምናነበው፤ ኢየሱስ ብዙ ተአምራትን እንዳደረገ ስለሚሰማ ተአምራትን ሲያደርግ ለማየትና፤ በተጨማሪም ደግሞ ብዙ ጥያቄዎችን ስለነበሩት ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ነበረ። ሄሮድስ ከኢየሱስ ማግኘት የፈለጋቸውን ነገሮች አላገኘም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በሄሮድስ ፊት አንድም ተአምር አላረገም፤ ደግሞም ለተጠየቀው ጥያቄዎች ለአንዱም እንኳን መልስ አልሰጠም። የፈለገውን ነገር ማግኘት ሳይችል ሲቀር ሄሮድስ ያደረገው ነገር፤ ከወታደሮቹ ጋራ ናቀው፣ አፌዘበት፣ የክብር ልብስ አልብሶ መልሶ ወደ ጲላጦስ ላከው።
3. የመጀመሪያው በቁ15 ላይ የሚገኘው እርሱ ራሱ መርምሮት ምንም ዓይነት ስህተት እንዳላገኘበት የሚናገረው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ወደ ሄሮድስ ተልኮ ሄሮድስም በእርሱ ላይ ምንም ዓይነት ስህተት ባለማግኘቱ መልሶ መላኩ ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ እዚያው ቁ15 ላይ ለሞት የሚያበቃ የፈጸመው ነገር እንደሌለም ይነግራቸዋል። እንዲፈታላቸው የጠየቁት በርባንን ነበረ። ከዚህ ሁኔታ የምማረው የሰው ልጅ ከጽድቅ ይልቅ ለዓመጽ ቦታ እንደሚሰጥ፣ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ለመምረጥ ወደኋላ እንደማይል ነው።
4. እነዚህ ሰዎች ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ ጲላጦስ የሰጣቸው ሶስት እድሎች እንደነበሩ ከቁ15፣ 20፣ 22 ላይ ማየት ይቻላል። የሰዎቹን የጥላቻቸውን ጥልቀት የሚጠቁሙን ሃሳቦች፤ ቁ23 ላይ ከበፊቱ ይልቅ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲሰቀል መጠየቃቸው፣ ጩኸታቸውም እየበረታ መሄዱ፣ ከኢየሱስ ይልቅ ነፍሰ ገዳይ የሆነውን በርባንን መምረጣቸውና የመሳሰሉት ሃሳቦች ይጠቁሙናል።
5. ኢየሱስን እየወሰዱት ያሉት ሰዎች (የካህናት አለቆች፣ ገዦች)፣ የቀሬናው ሰው ስምዖን፣ ኢየሱስ፣ ብዙ ህዝብ እና ደረታቸውን የሚደቁ ሴቶችን እመለከታለሁ። የኢየሱስ ሞት ለሃጥያታቸው መፍትሄ ስለሆነ ለቅሶ አያስፈልገውም፤ ነገር ግን ኢየሱስን ለመግደል ለተነሱት ሰዎች ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ሰው ሃጥያት ኢየሱስን በመስቀል ላይ ለመንጠልጠል ምክንያት ስለሆነው ለየራሱ ሃጥያት እንዲያለቅስ ነው ኢየሱስ እያስጠነቀቀ ያለው።
6. ኢየሱስ ለሚሰቅሉት ይጸልያል (ቁ34)፣ በኢየሱስ ልብስ እጣ ተጣጣሉ (ቁ34)፣ የሚሆነውን ተመልካቾች ነበሩ (ቁ35)፣ ገዥዎች ሌሎቹን አዳነ እስቲ ራሱን ያድን በማለት አፌዙበት (ቁ35)፣ ወታደሮቹ ያፌዙበት ነበረ፣ ሆምጣጤ አጠጡት (ቁ36)፣ ወታደሮቹ የአይሁድ ንጉስ ከሆንህ ራስህን አድን አሉት (ቁ37)፣ ከራሱ በላይም የአይሁድ ንጉስ የሚል ጲላጦስ ጽሑፍ አስቀመጠ (ዮሐ 19፡21)፣ አብሮ ከተሰቀለው አንዱ የስድብ ናዳ አወረደበት፣ እስቲ ራስህን እኛንም ደግሞ አድን አለው፣ ሌላኛው ወንጀለኛ ኢየሱስን በመንግሥቱ እንዲያስበው ለመነው፣ ኢየሱስም ዛሬ በገነት ከእርሱ ጋራ እንደሚሆን ነገረው።
7. እግዚአብሄር ያከናወናቸው ነገሮች፣ ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ላይ ጨለማ እንዲሆን ማድረግ፣ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መከፈል እና፣ ነፍስን በታላቅ ድምጽ ጮሆ ለአምላክ አሳልፎ መስጠት ናቸው። እኔ የሚመስለኝ ይህ ሁኔታ የኢየሱስን ጻድቅነት ብቻ ሳይሆን የዓለም መሲህ እንደሆነ ያስተማረውን ትምህርት ያረጋገጠለት በመሆኑና ለሃጥያቱ መልስ ሊሆንለት እንደሚችል ስለተረዳ ሳይሆን አይቀርም እላለሁ።
8. አብዛኛዎቹ የሸንጎ አባላት ፍላጎታቸው ኢየሱስን ማጥፋት ብቻ ሲሆን ይህ ሰው ደግሞ በኢየሱስ ላይ የወሰኑትን ውሳኔ ፊት ለፊት በመቃወም በኢየሱስ ወገን የሚቆም ሰው ስለነበረ ሥራውን ከባድ እንደሚያደርግበት የማያጠራጥር ሃቅ ነው።

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ ሉቃስ 24፡1-53 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወደ ኢየሱስ መቃብር የሄዱትን ሴቶች ግራ ያጋባቸው ሁኔታ፤ በቁ2 ላይ ሉቃስ የተናገረው ማንም ከፍቶ እንዳያወጣውና ከዚያም ኢየሱስ ተነሳ የሚል ወሬ እንዳይዘራ በተደረገው ጥንቃቄ የተቀመጠው ትልቅ ድንጋይ ተንከባሎ ማየታቸው ነበረ። ሴቶቹ በሁኔታው መደናገራቸው የማያስገርምበት ምክንያት፤ መላዕክቱ ለሴቶቹ ኢየሱስ በገሊላ ከእነርሱ ጋራ በነበረ ጊዜ ስለ ትንሳኤው የነገራቸውን ያስታውሳቸዋል፤ ያ በሆነ ጊዜም ቁ8 እንደሚነግረን እውነትም ኢየሱስ ነግሯቸው እንደነበረ ትዝ ይላቸዋል።
2. መላዕክቱ የተገለጡላቸው ሴቶች ቁጥር ቁርጥ ባለ መንገድ ባጥጻፍም እንኳን፤ ከቁ10 መረዳት እንደምንችለው በስማቸው የተጠቀሱ ሶስት ሴቶች ሲኖሩ፤ በተጨማሪ ደግሞ "ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች" ስለሚል፤ የእነዚህ ቁጥር ደግሞ በብዙ ቁጥር ስለጠራቸው ከሁለት ሊያንሱ እንደማይችሉ እናውቃለን፤ ስለዚህ በአጠቃላይ ቢያንስ ቢያንስ 5 ሴቶች ይሆናሉ። አንድ ሰው ቃዥ ቢባል እሺ፣ ነገር ግን አምስት ሰው ቃዥ ማለት ግን ሊቃዥ የማይመስል ነው። ጴጥሮስ እንዳልተባበረ በወሰደው እርምጃ እናያለን።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለ ነብይ እንደነበረ፤ እርሱም በእግዚአብሄርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ እንደነበረ፤ የካህናት አለቆችና፣ ገዥዎች ለሞት አሳልፈው እንደሰጡትና እንደገደሉት ነበረ ይነጋገሩ የነበረው። በእኔ አመለካከት ጓደኛሞቹ ቀድሞ የመሰላቸው ኢየሱስ እስራኤልን እንደሚቤዥ ሲሆን፤ ከአነጋገራቸውና ከድርጊታቸው ስናይ ግን ያ አመለካከት አፈር በልቶታል።
4. ሰዎቹ በመንፈሳዊ ህይወታቸው የሚገኙበትን ሁኔታ ለመግለጽ ኢየሱስ የተናገራቸው፤ "እናንተ የማታስተውሉ ሰዎች" እና "ልባችሁ ነብያት የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ" በማለት ነው የወቀሳቸው። በተለይ ሊናገራቸው የፈለገው በቁ26 ላይ የገለጸውን፤ ክርስቶስ መከራን ከተቀበለ በኋላ ወደ ክብሩ መግባት እንደሚኖርበት የሚናገረውን ትንቢት ነው። አለማመናቸውን ነቅፎ ካበቃ በኋላ፤ ወደ ቀደመው ቦታቸው ሊመልሳቸው ቃሉን ሲያስተምራቸው እንመለከታለን።
5. የሰዎቹ ዓይን እንደተከፈተና ኢየሱስን እንዳወቁት የምናየው አብረው እንጀራን ሲቆርሱ እንደሆነ ከቁ30 ላይ መረዳት እንችላለን። ኢየሱስ በመንገድ ላይ ከሙሴና ከነብያት እየጠቀሰ መጻሕፍትን ሲያስተምራቸው ይሰማቸው የነበረው ስሜት ልባቸውን እንደ እሳት ያቀጣጥለው እንደነበረ ነው የተናገሩት። የእግዚአብሄር ቃል በራሱ በህይወታችን ትልቅ ሥፍራ ሲኖረው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከኢየሱስ ጋራ ቅርብ በሆነ መንገድ ግንኙነት የማናደርግ ከሆነ የእርሱን ትክክለኛ ማንነት ማወቅ እንደማንችል ነው። ከኢየሱስ ጋራ የቅርብ ግንኙነት ሳይኖር፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ብቻ ሆኖ መገኘት ይቻላል።
6. በኢየሩሳሌም የነበሩትም ሆኑ ከኤማዖስ የተመለሱት ደቀ መዛሙርት በየበኩላቸው የኢየሱስ ከሞት መነሳት ያረጋገጡ በመሆኑ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ እርግጠኛነቱን ሲወያዩ ነበረ። ከኢየሱስ አነጋገር ከቁ38 እና 39 እንደምንረዳው እነዚህ ሰዎች መንፈስ ሥጋ ያለው ነገር እንዳልሆነና ሊታይ እንደማይችል ስላልገባቸው፤ ጌታ ይህንን ግልጽ ለማድረግ እጆቹንና እግሮቹን የተወጉትን እንዲመለከቱ ይንግራቸዋል።
7. በህግ፣ በነብያትና፣ በመዝሙር መጻህፍት ስለ ኢየሱስ ከተነገሩት ነገሮች እዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተፈጽሞ የምናገኘው ነገር፤ በቁ46 ላይ ገልጾ የነገራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ መከራን እንደሚቀበልና፤ በሶስተኛውም ቀን ከሙታን እንደሚነሳ ነው። በዚህ ቁጥር ላይ ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር፤ መጻህፍትን ማስተዋልና መረዳት እንዲችሉ አዕምሮአቸውን እንደከፈተላቸው ነው። እኛም ብንሆን የእግዚአብሄርን ቃል ለብዙ ዘመናት ልናነብና ልናጠና እንችላለን፤ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ አዕምሮን ካልከፈተ መረዳት እንደማይቻል እማራለሁ።
8. የደቀ መዛሙርቱ ድርሻ ሃይል እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም መቆየት እንደሚኖርባቸውና፣ ሃይል ከተቀበሉ በኋላ ደግሞ ለእርሱ ምስክር መሆን እንደሚጠበቅባቸው የተናገረ ሲሆን፤ ኢየሱስ የራሱ ድርሻ አድርጎ የተናገረው ነገር ደግሞ አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ማለትም የወንጌልን አገልግሎት በእነርሱ ውስጥ የሚሰራውን መንፈስ ቅዱስን መላክ ነው።